# አዲስ ዘመን

እንድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 338 ነሐሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## “ባለፉት አራት ዓመታት ሲካሄድ የቆየው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ተጨባጭ ውጤት አምጥቷል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አራት ዓመታት ሲካሄድ የቆየው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ተጨባጭ ውጤት አምጥቷል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሐረር ከተማ በተለምዶ ሃማሬሳ በሚባለው የሐረሪ ባህል ማዕከል ቅጥር ግቢ ችግኝ በመትከል አረንጓዴ አሻራቸውን ትናንትና አኑረዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት የአረንጓዴ አሻራ ሌጋሲ ሥነምህዳሩን በመጠበቅ ረገድ ውጤት ማስገኘቱን ጠቁመዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ለኢትዮጵያ አዋጭ መሆኑ በብዙ ማሳያዎች ተረጋግጧል፤ በተለይም ጠፍቶ የነበረውን የሃረማያ ሃይቅ የመለሰ ስራ ተከናውኗል ብለዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ሌጋሲ ውጤት ስለማምጣቱ ከሐረርጌ ሕዝብ በላይ ምስክርነት የሚሆን የለም ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ለሁለት አስርት ዓመታት ደርቆ የቆየው የሃረማያ ሀይቅ

‹‹ባለፉት አራት ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል






## የግድቡ ኃይል ማመንጨት መብታችንን የማስመለስ መንፈስን ማደሱ ተነገረ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የህዳሴው ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ለኢትዮጵያውያን ኃይል ከማመንጨት አልፎ ለመላ ኢትዮጵያውያን የሀገር አንድነትን፣ የሕዝቦች መተሳሰብንና መብታችንን የማስመለስ መንፈስን አድሷል ሲል አቶ ሙሃመድ አልአሩሲ ተናገረ፡፡

የዓባይ ግድብ ተሟጋችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆነው ሙሐመድ አል አሩሲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ 3ኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ስኬት ነው፡፡

እንደ አል አሩሲ ገለጻ፣ የህዳሴው ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ከማመንጨት አልፎ የአገር አንድነትን፣ የመተሳሰብና መብታቸውን የማስመለስ መንፈስን አድሷል ብሏል፡፡

ኢትዮጵያውያን በአላህ እርዳታ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው እድገት ያላቸውን ቁርጠኝነት እጥፍ ድርብ አድርጎ ጨምሮታል ያለው አልአሩሲ፤ በህዳሴ ግድብ ያስመዘገብናቸው ድሎች የአገራችንን ታላቅነት፣ የሕዝባችንን ጀግንነት፣ የራዕያችን ስኬት፣ የሚያሳይ እና የህዳሴያችን ጠላቶች ላይ ያሸበረቀ ድል ያስገኘ መሆኑን መስክሯል ብሏል፡፡

የግድቡ ኃይል ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል





## “በስፖርቱና በዓባይ ግድብ የተገኘው ድል ሕዝብ ከተባበረ ውጤት ማምጣት እንደሚችል ያሳየ ነው”

- አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በስፖርቱና በዓባይ ግድብ ላይ የተገኘው ድል ሕዝብ ሲተባበር ውጤት ማምጣት እንደሚችል በተግባር ያሳየ ነው ሲሉ የቀድሞው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ገለጹ፡፡

አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው በየዘርፉ በተገኙት ድል የተሰማቸውን ደስታ በመግለፅ፤ ለመላው ኢትዮጵያዊያን የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲተባበርና በጋራ ሲሰራ የተሻለ ውጤት ይገኛል። በአትሌቲክሱና በህዳሴ ግድብ

በስፖርቱና በዓባይ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል






## ኢትዮጵያ በህዳሴ ግድብ እያከናወነች ያለው ሥራ ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ተምሳሌት መሆኑ ተለጸ

ገጽ 5






እመቤት ተፈሪ



አቶ መስፍን ኃይለሥላሴ



አቶ ደስታ ገብረእግዚያብሔር

# በስፖርቱና በህዳሴ ግድቡ የተገኙት ውጤቶች በሁሉም ዘርፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተጠየቀ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያው በዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድርና በህዳሴ ግድቡ ግንባታ ያገኘቻቸው ውጤቶች በሁሉም ዘርፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ጠየቁ።

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን ከሰጡ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እንደገለጹት፣ በስፖርቱ በተለይም በአትሌቲክሱ ዘርፍ እንዲሁም በታላቁ የህዳሴ ግድብ ላይ የተገኙት አመርቂ ውጤት በተለያዩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎችም ላይ ሊጠናከር ይገባል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወጣት እመቤት ተፈሪ፤ በአስራ ዘጠነኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር ውጤቶችና በህዳሴው ግድብ ስኬት እንደ አንድ ዜጋ ደስተኛ ነኝ። በየዘርፉ የተመዘገበው ውጤት በተለያዩ አገራዊ የልማት ስራዎችም ሊጠናከር ይገባል ስትል አስተያየቷን ሰጥታለች።

በየአካባቢው የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በየደረጃ እየፈተሹ በመቅረፍ በስፖርትና በህዳሴው የተገኘውን ድል መድገም ይገባል ያለችው ወጣቷ፤ ለዚህም አመራሩም ሆነ ሕብረተሰቡ ቀዳሚውን ሚና መጫወት እንዳለበት ነው የገለጸችው።

በአትሌቲክሱና በህዳሴ ግድቡ ግንባታ የታየውን የአንድነት፣ የመተሳሰብንና በጋራ የመቆም መንፈስ በማዳበር አገርን ለተሻለ ውጤት ማብቃት ያስፈልጋል። ለዚህም እያንዳንዳችን ሃላፊነታችንን መወጣት እንደሚገባ ወጣት እመቤት አስተያየቷን ሰጥታለች።

በመምህርነት ሙያ አገራቸውን ያገለገሉት አቶ መስፍን ኃይላሥላሴ በበኩላቸው፤ በስፖርቱና በህዳሴው ግድብ ላይ የታየው ውጤት ደስ እንዳሰኛቸው በመግለጽ፤ የተገኙትን ውጤቶች የበለጠ አመርቂ ማድረግ የሚቻለው እንደአገር በሚያጋጥሙት ችግሮች ላይ ድል ማስመዝገብ ሲቻል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ስፖርት ቀድሞም ታሪኳ ከፍ ያለ ነው፡፡ አሁን ደግሞ ወጣቶቹ የበለጠ ከፍ አድርገውታል። በቀጣይ የስፖርቱንና የህዳሴ ግድቡን ስራዎች ስኬቶችን በማጠናከር በሁሉም ዘርፎች ያሉ የልማት ስራዎችን የተሻሉ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። በተለይም ድህነትን በመከላከልና ኢኮኖሚያችንን በማጠናከር ረገድ ሕዝቡና መንግሥት የጀመሯቸውን የጋራ ልማት ስራዎች ማጠናከር ይኖርባቸዋል ብለዋል።

አቶ መስፍን እንደገለጹት፤ እንደ አገር አሁን ያሉት የልማት ስራ አቅጣጫዎች ጥሩ ናቸው። እነዚህም የልማት አቅጣጫዎች ከግብ በማድረስ የአብዛኛውን ማሕበረሰብ ችግር መፍታት ይቻላል። ይህ ሲሆን በስፖርቱም ሆነ በህዳሴው ግድብ የተገኙ ድሎችል የበለጠ ትርጉም ይኖራቸዋል።

በአትሌቲክሱና በታላቁ ህዳሴ ግድቡ ስራ ላይ በተገኙ ስኬቶች ሳንኮፈስ በተለያዩ የልማት መስኮችም የበለጠ ውጤት ለማምጣት በርትተን መስራት ይኖርብናል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያውያን እራስን በመከላከልና በጥንካሬ የታወቅን ነን ያሉት አቶ መስፍን፣ ባለን ጥንካሬ፣ ወኔ፣ ጀግንነት ደግሞ የአገራችንን ታላቅነት በአትሌቲክሱና በህዳሴ ግድባችን አሳይተናል። ይህን አጠናክረን በማስቀጠል የአገራችንን ሰላም፣ ልማት፣ ዕድገትና ብልጽግና ጉዟችንን የሚገታ እንደሌለ ደጋግመን ልናበስር ይገባናል ብለዋል፡፡

ሌላኛው የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ ደስታ ገብረእግዚያብሔር በበኩላቸው፤ በስፖርቱና በህዳሴው ግድብ ስራ የተገኙትን አመርቂ ውጤቶች በኢኮኖሚውም ሆነ በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፉ ልንደግመው ይገባናል ሲሉ ተናግረዋል።

ድሉና ስኬቱ ቀጣይነት እንዲኖረው መንግሥትና ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ኃላፊነት በያለበት ሊያበረክት እንደሚገባም ጠቁመው፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድነቱን በማጠናከር የወደፊቷ ኢትዮጵያ የለማች፣ የበለጸገችና ለሰዎች መኖሪያ ምቹ የሆነች የማድረግ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በስፖርቱ ዓለምና በህዳሴ ግድቡ የግንባታ ሂደት ስኬቶች በሁሉም ዘርፎች በተለይም በልማት ስራዎች ሊደጋገሙና ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ሲሉ አቶ ደስታ አክለው ተናግረዋል፡፡

## ሚኒስቴሩ የወደመ ትምህርት ቤት መልሶ ለመገንባት የመሰረት ድንጋይ አኖረ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ጭፍራ፡- ትምህርት ሚኒስቴር በአፋር ክልል ጭፍራ ወረዳ በጦርነቱ የወደመውን የጭፍራ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መልሶ ለመገንባትና በዛው አካባቢ አዲስ የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማሰራት የመሰረት ድንጋይ አኖረ።

የመሰረት ድንጋዩን ያስቀመጡት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደገለጹት፤ ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ወያኔ የአፋር ሕዝብ ጥራት ያለው ትምህርት እንዳያገኝ ሞክሯል፡፡

በአፋርና አማራ ክልል በጦርነቱ የፈረሱ ትምህርት ቤቶችን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአዲስ መልክ እየገነባ እንደሚገኝ የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ በአፋር ክልል ጭፍራ ወረዳ የፈረሰው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በአዲስ ቦታና በአዲስ መልክ በስልሳ ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ እንደሚገነባ አመልክተዋል።

ትምህርት ቤቱ ከስፖርት ማዘውተሪያ ጀምሮ፣ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ የእርሻ ቦታና ሌሎችም ለመማር ማስተማር ሂደት አጋዥ የሆኑ ግብአቶችን ያካተተ መሆኑንም ጠቁመዋል። ብዙ ሳናወራ ብዙም የመሰረት ድንጋይ ሳናስቀምጥ ስራችንን እንሰራለንም ብለዋል።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ እነዚህን ትምህርት ቤቶች በመገንባት ሂደት የሰዎች ለሰዎች ድርጅት ትልቅ እገዛ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ትምህርት ቤቱ ግንባታው በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል ።

የአፋር ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ቁለማ አቡበከር በበኩላቸው ክልሉ በጎርፍ፣ በኮሮና፣ በጦርነትና በሌሎች በትላልቅ ችግሮች ያለፈ መሆኑን ገልጸው ችግሮቹን ለመቅረፍ የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን ተናግረዋል።

በተለይ ጦርነቱ በሕዝቡ ላይ ጥሎ ያለፈውን ጠባሳ ለማጥፋትና ችግሮቹን በጋራ ለማሸነፍ በፌዴራል ደረጃ ትልቅ እገዛ እየተደረገ እንደሚገኘ አስታውቀዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር ጭፍራ ወረዳ ላይ ትምህርት ቤት ለገንባት የሚያደረገውን ጥረት እንደሚያደንቁም ገልጸዋል።

# የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲጠናከር መንግሥት ጥረት እያደረገ መሆኑ ተገለጸ

### - ኢንስቲትዩቱ በ12 የሙያ ዘርፎች 296 ተማሪዎችን አስመረቀ

**ስምስም መንግሥቱ**

አዲስ አበባ፡- የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ዘርፉ በሚጠይቀው የሰለጠነ ሰው ኃይል እንዲጠናከር መንግሥት ጥረት እያደረገ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት በመደበኛና በተከታታይ ትምህርት በ12 የተለያዩ ዘርፎች ያሰለጠናቸውን 296 ተማሪዎች ትናንትና አስመርቋል።

በምርቃቱ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ነቢሃ መሐመድ እንደገለጹት፤ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በክህሎትና በሥነምግባር በታነጹ ባለሙያዎች እንዲጠናከር ለማድረግ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል።

ኢትዮጵያን ከተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም ሀብቶቿን አልምታ የተሻለ ገቢ እንድታገኝ በዘርፉ ብቁ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ መንግሥት በቱሪዝም ዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያደርገውን ጥረት በተለያዩ አካባቢዎች ላይ አጠናክሮ መቀጠሉን ጠቁመዋል።

በተለይም መንግሥት ተልዕኮውን በማስፋት በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚጠበቅበትን እየተወጣ መሆኑንም



ወ/ሮ ነቢሃ መሀመድ እና አቶ ጌታቸው ነጋሽ

አመልክተዋል።

የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በአማካይ ከአስር ሥራ አጥ ዜጎች ለአንዱ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል ዘርፍ መሆኑን የዓለምአቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳይም የጠቆሙት ወይዘሮ ነቢሃ፤ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርም ዘርፉን በተማረ የሰው ኃይል ለማጠናከር የሚያደርገውን ጥረት እያጎለበተ መሆኑን ገልጸዋል።

በሀገራዊ የሪፎርም ማሻሻያ ውስጥ ከተካተቱት አንዱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው መሆኑንና በዘርፉም መንግሥት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ለሰልጣኞች የተግባር ሥልጠና እያመቻቸ መሆኑን ጠቁመው፤ በአዲስ አበባ ከተማ የእንጦጦ፣የወዳጅትነትና የአንድነት ፓርኮችን ለቱሪዝም ዘርፉ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ እያደረጉ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች መካከል መሆናቸውን ተናግረዋል።

ተመራቂዎችም በትምህርት ቆይታቸው የቀሰሙት ዕውቀት ለዘርፉ በማዋል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡም መልዕክት አስተላልፈዋል።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በበኩላቸው፤ ኢኒስቲትዩቱ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በማፍራት በየአመቱ ብቁ ባለሙያዎችን እያፈራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ያለው የቱሪዝም ሀብትና ኢንዱስትሪው የሚፈልገው የሰለጠነ ባለሙያ የተመጣጠነ አለመሆኑን ገልጸው፤ ኢኒስቲትዩቱ ይህንን ክፍተት ለሙላት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን አመልክተዋል።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት በመደበኛና በተከታታይ ትምህርት በተለያዩ ዘርፎች ያሰለጠናቸውን 296 ተማሪዎች ትናንትና ሲያስመርቅ፤ ከ296 ተመራቂዎች መካከል 186ቱ በደረጃ አራት፣ 110ሩ ደግሞ በደረጃ ሶስት የሰለጠኑ መሆናቸው ታውቋል።

ኢኒስቲትዩቱ ለ54ኛ ጊዜ ያስመረቃቸው ተማሪዎች በማስጎብኘት፣ በእንግዳ አቀባበል፣ በምግብና መጠጥ ዝግጅት፣ በቤት አያያዝ፣ በአጠቃላይ በ12 የሙያ ዘርፎች የሰለጠኑ ናቸው። በትምህርታቸው ብልጫ ላመጡ ተመራቂዎችም የዋንጫና የሜዳሊያ ሽልማት ተሰጥቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በወጣቶቻችን አኩሪ ጥረት ከጉባ እስከ ካሊ ድል በድል!

አገር በሰው ትሰራለች፤ የየዘመን ገጿም በየዘመኑ በሚሰሯት ሰዎች የእጅና አዕምሮ ውጤት ላይ ተመስርቶ ይሰላል:: ምክንያቱም አገር በትውልዶች ቅብብሎሽ የምትቀጥል፤ በሕዝቦቿ ሕብረትና እሳቤ አማካኝነት ከፍ የምትል ናትና:: የዛሬዋ ኢትዮጵያም የትናንት አባቶች የሰሯት ብትሆንም፤ በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች አሻራ እያረፈባት በመውጣትና መውረድ ውስጥ እየተራመደች ለዚህ የበቃች ናት:: ትናንት ጠላት ሊደፍራት ሲቋምጥና ለወረራ ሲሰማራ ድባቅ መትተው የመለሱ ጀግኖች በደም መስዋዕትነት የቀረጿትና ዛሬ ያደረሷት ኢትዮጵያ፤ በኋላም በሰላሙ መድረክ በላባቸው ከፍ አድርገው የሰቀሏት እንቁ አትሌቶች ከፍታዋን አስቀጥለው እነሆ የደስታችን ጅረት እንዳይቋረጥ አድርገዋል::

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ በብዙ ችግር ውስጥ ባለችበት ጊዜ፣ ወጣቶች በስሜት እየተገፉ ለጥፋት ሃይሎች መሳሪያነት በሚታጩበትና ለተልዕኳቸው መሳሪያ ሆነው እያገለገሉ ባሉበት ሰዓት፤ ሀገርን ወክለውና የአገርን ሰንደቅ ዓላማ በአደራ ተረክበው በዓለም አደባባይ ስለ ኢትዮጵያ ነጭ ላብ እያፈሰሱ መድከምና መፋለምን የመረጡ እንቁ ወጣቶችን መመልከት ተችሏል:: ወደ ኮሎምቢያ ካሊ ለማቅናት የቀደሙ አርዓያዎቻቸውን ተከትለው በሙሉ ልብና እምነት ለድል አድራጊነት ዝቅ ብለው ሰንደቋን የተቀበሉ የሃያ ዓመት በታች ተፋላሚ አትሌቶች፤ ዝቅ ብለው የተቀበሉትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው ለማውለብለብና ለብሰው ለመድመቅ በቅተዋል::

ቃል በተግባር እንዲሉ፤ አሸንፈው በድል ለመመለስና ኢትዮጵያን ከፍ ለማድረግ የሰጡትን ቃል በተግባር ለውጠው በስድስት ወርቅ፣ በአምስት ብር እና በአንድ ነሃስ በድምሩ 12 ሜዳልያዎችን በመሰብሰብ ኢትዮጵያን ከዓለም በሦስተኛ፣ ከአፍሪካ ደግሞ በአንደኛ ደረጃ ላይ በከፍታ አስቀምጠው በድል ተመልሰዋል:: የእነዚህ ወጣትነት ያልበገራቸው፣ አፍላነት ከሀገር በላይ ለግላቸው እንዲያስቡ ያላደረጋቸው፣ ጥቅም ከአገር ክብር ያልገዘፈባቸው እነዚህ በኮሎምቢያ ካሊ ላይ የደመቁ ወጣት አትሌቶች፤ ኢትዮጵያን ከፍ አድርገው በድል ሲመለሱ የጀግና አቀባበል ተደርጎላቸዋል:: በዚህ ወቅት ነበር "እናንተ አንበሳ ናችሁ፤ አንገታችሁ ላይ ያለውም አንበሳ አስመስሏችኋል፤ አንበሳነታችሁንም አረጋግጣችሁበታል" ሲሉ በአቀባበሉ ላይ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ ቀጄላ መርዳሳ የአትሌቶቹን ነግሶ ሀገር አንጋሽነት የመሰከሩት::

እውነታው ይሄ ነው፤ ለሴረኞች ተግባር ተገዢ የሆኑ ከሀገር ይልቅ ለግል ጥቅም ተገዝተው ነገን ሳይሆን ዛሬን ለመኖር ሲሉ መኖራቸውን የሚነጠቁ፣ ሕዝባቸውንም የጎዘን እንባ የሚያስነቡ ወጣቶች በአንድ በኩል የተሰማሩበት፤ ስለ ኢትዮጵያ ሲሉ ወጣትነታቸውን የሚገብሩ እንቁ ወጣቶች ደግሞ ከጉባ እስከ ካሊ ኢትዮጵያን አሸናፊ አድርገው ኢትዮጵያውያንን የደስታ እንባ የሚያራጩና በደስታ የሚያስቦርቁ በሌላ ጎራ መኖራቸው:: እነዚህ ሁለት የኢትዮጵያ የማሕጸን ፍሬዎች ታሪክ እንደየስራቸው የሚዘክራቸው ቢሆንም፤ አሁናዊ ገድላቸው ሲነሳ ከበዛው እንክርዳድ ጥቂቶቹን ስንዴዎች በዓርአያነታቸው ማንሳቱ አይቀሬ ነው::

ምክንያቱም በኮሎምቢያው ሻምፒዮና የነገሱት ጀግና አትሌቶች ስለ ኢትዮጵያ ከሃያላኑ ጋር ተፋልመው ኢትዮጵያን አሸናፊ አድርገዋልና የድላቸው መንገድና ምስጢር ለተቀረው ወጣት አስተምህሮውና አርዓያነቱ የላቀ ነው:: ምክንያቱም የዘር ካባ ደርበው ስለ ቡድኖች ሕልውና ሲሉ በሕዝብና አገር ላይ ጥላቻን በመስበክ በውጭ አገራት በየአደባባዩ ጥፋትን ሲደሰኩሩ የሚውሉ ሆድ አደር ወጣቶችን በምንመለከትበት በዚህ ወቅት፤ በዓለም መድረክ ስለ ሀገርና ሕዝብ ክብርና ከፍታ ሲሉ ሙሉ አቅማቸውን ሰጥተው ሰንደቃቸውን ለድል የሚያነሱ፤ በሰንደቃቸው ላብና እንባን የሚያብሱ ወርቃማ ወጣቶች አርዓያነታቸው በጉልህ ሊነገርም፣ ሊዘከርም የሚገባው ነው::

በተመሳሳይ የዘመናትን የኢትዮጵያውያንን ህልምና ቁጭት ወደ ተግባር ለመለወጥ ዓመታትት በበርሃ ከትመው፤ ወጣትነታቸውን ሳይኖሩ ስለ አገርና ሕዝብ ፍላጎት መሳካት በጉባ በረሃ ከትመው ህዳሴ ግድቡን ከንድፍ ወደ መብራት የለወጡ ብርቅዬ ወጣቶች ታይተዋል:: በዚህም ረገድ ቢሆን ለራስና ለቡድን ጥቅምና ሕልውና ሲሉ በቡድንም ሆነ በተናጥል፣ በግልጽም ሆነ በሽምቅ ሕዝብን የሚያደሙ፣ አገርን ለህልውና አደጋ የሚያጋልጡ ጥቅመኛ ተገዢ ወጣቶችን በምናይባት ሀገራችን፤ የጉባዎቹን ወጣቶች በህዳሴው ግድብ እውን መሆን ውስጥ ያሳለፉትን ያልተኖረ ወጣትነታቸውን ሳያስቡ ዕውቀታቸውን ገብረው ህዝብን በደስታ የማስጨፈር፣ አገርን በአይበገሬነት ሰገነት ላይ የማኖር ገድል በአስተማሪነቱ መተረክ፣ ሰንዶም ለትውልድ ማኖር የተገባ ነው::

በዚህ መልኩ ከጉባ እስከ ካሊ የተዘረጋው የወጣቶች የአሸናፊነት ገድል፣ ኢትዮጵያን ከችግሮቿ ባሻገር ያለው ህልሟ እንዲገለጥ፣ የጠለሸው ገጿ እንዲነጻ፣ የተረበሸው የሕዝቧ ስሜት እንዲረጋጋና በአንድ ስሜት ወደ አንድ የብልጽግናና አንድነት መስመሩ እንዲመለከት ያደረገ ታላቅ ተግባር ነው:: ይህ ተግባር ነው አገርን ከፍ ያደረገ፤ ሕዝብን በደስታ ያሰከረውና የኢትዮጵያን የነገ መንገድ ለመመልከት ያልቻሉትን ቆም ብለው እንዲያስቡ ያስገደደ:: ታዲያ ከእነዚህ ወጣቶች ገድል በላይ ለዛሬው ትውልድ አርዓያ የሚሆን ምን ሊገኝ? በመሆኑም ወጣቶች ከእነዚህ ሊገነዘቡ የሚገባው የወጣትነት ጊዜያቸውን ስለ ሀገርና ሕዝብ ማዋል፤ በተሰማሩበት መስክ ሁሉ ለስኬት መትጋት እንዳለባቸው ብቻ ሳይሆን፤ ለአገርና ሕዝብ የሚከፈል ዋጋ ክፍያውም ክፍያ ያለው መሆኑን ነው!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ስኬቶቻችንን የችግሮቻችን መሻገሪያ እናድርጋቸው

**በየኔነው ስሻው**

ስኬት የበርካታ ትግል ፍሬ ነው፤ ስኬት ለላቀ ለውጥና ከፍታ እንደ መስፈንጠሪያ አንጓም ነው፤ ስኬት የትናንት ልፋት፣ የዛሬ እረፍት እና የነገ የተሻለ ሕልም የተጋመዱበት ህያው የሰው ልጆች የከፍታ ማማ ነው:: በተለይ ደግሞ የስኬት ጉዞው በውስብስብና በበዙ ፈተናዎች ውስጥ ታልፎ ሲገኝ እጅጉን የሚያኮራ ብቻ ሳይሆን፤ ስለነገው የላቀ የከፍታው የስኬት ሰገነት ላይ ለማረፍ ለሚደረገው ትግልና ጥረት ስንቅ ሆኖ ያገለግላል:: ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን እንደ ምስክርም፤ እንደ አብነት ሊጠቀሱ ተገቢ ነው:: እንዴት ቢሉ፤ ከብዙ በጥቂቱ እንዲህ ብሎ ማንሳት ይቻላል፡-

የመጀመሪያው ጉዳይ ኢትዮጵያውያንን ስኬታማና የስኬታማነት ማሳያ የሚያደርጋቸው የግዛት ነጻነታቸው ነው:: ይህን ነጻነታቸውን በቀልድ አላገኙትም፤ ይልቁንም በደምና ሕይወት ዋጋ ከሶስት ሺህ ዘመን በላይ ይዘው የዘለቁት እንጂ:: የመጀመሪያው ድላቸው ለሁለተኛው አቅም እየፈጠረ፤ የቀደሙቱ ለተከታይ ልጆቻቸው ጀግንነትና ድል አድራጊነትን እያወረሱ፤ የነጻነታቸውን የስኬት መንገድ ሳያዛንፉ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ነጻነት ለናፈቃቸው ሕዝቦች ሁሉ ምሳሌ ሆነው እነሆ ዛሬም አሉ::

ይሄ ስኬታማ የነጻነት ጉዟቸው ደግሞ ለሌሎች ድሎቻቸውና የስኬት መንገዶቻቸው ፈር ቀዳጅ ሆኖ አገልግሏቸዋል:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ ስትባል ያልተደፈረች ታላቅ አገር መሆኗ በዓለም መገለጡ፤ ኢትዮጵያውያንም አገርን ሳያስደፍሩ፣ ወገንን ቅኝ ሳያስገዙ በአሸናፊነት የስኬት መንገድ ላይ ጸንተው የቆሙ ሕዝቦች ሆነው መታየታቸው ትውልዱ ከአሸናፊነት ሌላ ማሰብን እንዳይለምድ አድርጎታል:: የዚህ አንዱ ማሳያ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ደጋግማ የነገሰችበት ስፖርት በተለይም አትሌቲክስ ነው:: የኢትዮጵያውያን አትሌሎች በተሳተፉባቸው መድረኮች ሁሉ ድል አድርገው ሰንደቃቸውን ከፍ ባደረጉ ጊዜ ማንባታቸው፤ በውድድር ሂደቱም ስለ አገር አሸናፊነት እንጂ ስለ ግል ሜዳልያ ባለቤትነታቸው ሳይሳሱ ተባብረው የአረንጓዴ ጎርፍ ስማቸውን መትከላቸው የዚህ ያለመሸነፍ ሰብዕና ገጻቸው ነው::

ይህ በነጻነት የነገሰው ማንነት በአትሌቶቻችን ልብና ማንነት ላይ የፈጠረው አዎንታዊ ገጽ ቢኖርም፤ የኢኮኖሚ ነጻነቷ ያልተረጋገጠ አገርና ሕዝብ ሙሉ ነጻነቱ ተረጋግጧል፤ ስኬታማ መንገዱም ከሚፈለገው ቦታ ላይ አርፏል ማለት አይቻልም:: ለዚህም ነው የዘመናት ሕልማችን የነበረውን ዓባይ ገድበን ወደ ኤሌክትሪክ መለወጥ የቻልነው፤ ከስንዴ ጥገኝነታችን ለመላቀቅም እጅን በአፍ ያስጫነ የስንዴ ልማት ስራ ውስጥ የገባነው፤ ዓለም እየተፈተነችበት ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ታሳቢ በማድረግም ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ነድፈን በአራት ዓመት ከሃያ ቢሊዮን በላይ ችግኝ መትከል የቻልነው::

እነዚህን ተግባራት ጀምረን ለስኬት ስናበቃ ግን ያለ ችግር አልነበረም:: ይልቁንም በውስጥ ባንዳዎች፣ በውጭ የኢትዮጵያን እድገትና ብልጽግና የማይሹ ታሪካዊ ጠላቶች እጅጉን የበረታ ፈተና ገጥሞን፤ አገር የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ እስከመግባት የደረሰችበትን አስጨናቂ ሁኔታ ጭምር ተቋቁሞ በማለፍ እንጂ:: የሕዳሴው ግድብ ዛሬ ላይ ሶስተኛ ዙር ውሃ ሲይዝ እና ሁለት ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት ሲጀምሩ፤ የግብጽን ሁሉን አቀፍ የማደናቀፍ ሩጫ በማክሸፍ፤ የአሸባሪው ሕወሓት ዘመን የብዝበዛና የዘረፋ ተግባር ታሪክ በማድረግ፤ የሕዝቦችን ያልተቋረጠ ድጋፍ በማስቀጠልና ኃይል በማድረግ ነው:: የስንዴ ልማትና የአረንጓዴ አሻራ ስራዎችም ቢሆኑ፤ ከሰላምና ጸጥታ ጋር ተያይዘው የተስተዋሉ በርካታ ፈተናዎች ውስጥ በተደረገ ትጋት ነው::

እነዚህ በፈተና ውስጥ የተገኙና እየተገኙ ያሉ ስኬቶች፣ ከስኬትነት ባለፈ ዛሬ ላይ ከችግሮች እንዴት ከፍ ብሎ ውጤት ማግኘትን፤ ውጤትና ስኬቶችንም እንዴት ለችግሮች መሻገሪያ ማድረግ እንደሚቻል የሚያስተምሩ ናቸው:: ለምሳሌ፣ የህዳሴው ግድብ ከነበረበት ችግር ተላቅቆና የእነ ግብጽና ግብራበሮቿን ሴራ አሸንፎ የመጀመሪያ ዙር ሙሌት ሲከናወን የነበረው ስሜት ኢትዮጵያውያን የነበረባቸውን ወቅታዊ ችግር መሻገሪያ ሃይል ሆኖ ነበር:: ሁለተኛው ዙር ውሃ ሲያዝና የመጀመሪያው ተርባይን ሃይል ማመንጨት ሲጀምር ደግሞ በሕልውናቸው ላይ የተደቀነው አደጋ ሳይበግራቸው ደስታቸውን የገለጹበት፤ የሕልውና አደጋ የሆነባቸውን ሃይል በአንድ ተሰባስበው እንዲያስወግዱ ያጎናጸፋቸው ብርታት ቀላል አልነበረም::

ይህ ሁሉ ሆኖ እያለም፤ ዛሬም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በበዛ ፈተና ውስጥ ይገኛሉ:: የሰላምና ጸጥታ ስጋትን የደቀኑ በርካታ ገፊ ምክንያቶችን አሸንፎ መውጣት የዚህ ዘመን የቤት ሥራ ነው:: የኢኮኖሚ እድገትን አስመዝግቦ የዳቦ ጥያቄን መመለስና እንደ ቋጥኝ የተጫነውን የኑሮ ውድነት ማሸነፍ ተደማሪ ሸክም ሆኗል:: በዘርና ሃይማኖት በመከፋፈል ኢትዮጵያውያንን ነጣጥሎ አገር ለመበተን እየሰሩ ያሉ ድኩማንን አደብ ማስያዝና በህብረ ብሔራዊነት የተገነባ አንድነትን ይዞ መዝለቅም ሌላው አቅምም፣ ስሜትም የሚፈትን ጉዳይ ነው::

በዚህ ረገድ አትሌቶቻችን በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና፣ እንዲሁም ከ20 ዓመት በታች ሻምፒዮና ላይ ያስመዘገቡት ድልና ስኬት ትልቅ አቅምና ስንቅ ሆኖናል:: ይሄ አቅማችን ሳይደክም፣ ስንቃችንም ሳይመነምን ዛሬ ደግሞ በግብርናው ስንዴን በማምረት፤ በሕዳሴው ግድባችን ደግሞ ተጨማሪ ኃይል በማመንጨት ስኬታችንን ከፍ አድርገናል:: በዚህም አገራዊ ስሜታችንን አሙቀን አንድነትና ብርታትን ተጎናጽፈናል:: ለነገ የብልጽግና ጉዟችንም ተጨማሪ ጉልበት ሰጥተውናል:: እዚህጋ ልንገነዘበው የሚገባው ጉዳይ ግን፤ በዚህ መልኩ በየዘርፉ የምናገኛቸው ስኬቶች ከስኬትም በላይ መሆናቸውን ነው::

ምክንያቱም እነዚህ ስኬቶች ፈተናዎችን አሸንፈን ያስመዘገብናቸው፣ ዳግም ያለመንበርከክ ጉዟችን ቀጣይነት ማሳያዎች ናቸው:: እናም ችግሮች ከስኬት መንገዳችን የማያግዱን፤ የጥፋት መልዕክተኞች የሴራ ትብብር ከጉዟችን የማያስቀሩን መሆናቸውን ያረጋገጥንባቸው ናቸው:: ሆኖም ይህ የአሸናፊነት ጉዞ ያደረሰን የስኬት ደረጃ በቂ አይደለም፤ እናም የብልጽግናችን ዋስትና የሚሆኑ ሌሎች ታላላቅ ስኬቶችን ማስመዝገብ የግድ ይላል:: ይሄ ደግሞ እንደ ትናንቱ ሁሉ ፈተና የማያጣን፤ ይልቁንም በስኬት ጉዞ ከፍታችን ልክ ከፍ ያሉ ችግሮች የሚገጥሙን መሆኑ እሙን ነው:: ለዚህ ደግሞ ትናንት ችግሮችን የተሻገርንባቸውን ልምዶች በመቀመር፤ በችግሮች ውስጥ ሆነን ያስመዘገብናቸውን ስኬቶች የነገ ችግሮቻችን መሻገሪያ አቅም አድርገን ልንጠቀምባቸው ይገባል:: ይሄን ስናደርግ ስኬቶቻችን ዘላቂ፤ ብልጽግናችንም እውን ይሆናሉ::

ETHIOPIAN


# እንኳን ደስ አለን!

የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት በመጠናቀቁ እንዲሁም የ2ኛ ተርባይን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ስራ በመጀመሩ የተሰማንን ደስታ እንገልጻለን።

ድርጅቱ እንደወትሮው ሁሉ የአገራችንን የወጪና ገቢ ዕቃዎች በባህርና በየብስ በማጓጓዝ የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነት በብቃት እየተወጣ የሚገኝ ሲሆን የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ዕውን ይሆን ዘንድ ከግዙፍ እስከ አነስተኛ ቁሶች በባህርና በየብስ የማጓጓዝ ስራ በተሳካ ሁኔታ በማከናወናችን ክብር ይሰማናል። በሀገሪቱ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ዕውን መሆን ላይ ቀጣይም አበርክቶአችንን አስፍተን የምንቀጥል መሆኑን እየገለጽን በአፍሪካ በፍላግሺፕ አገልግሎት ብቸኛ እንደመሆናችን የሀገር ኩራት እንደሆን እና በልህቀት እንደምንቀጥል ስንገልጽ በታላቅ ዕምነት እና ክብር ነው።




በድጋሚ
እንኳን ደስ አለን!






የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት
**ለጥረትዎ እሴት እንጨምራለን!**

ዜና

# ኢትዮጵያ በህዳሴ ግድብ እያከናወነች ያለው ሥራ ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ተምሳሌት መሆኑ ተለጸ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በህዳሴ ግድብ እያከናወነች ያለው ሥራ ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ሠርተው መልማት እንዳለባቸው የሚያሳይ ትልቅ ተምሳሌት መሆኑ ተገለጸ::

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ረዳት ፕሮፌሰር ያየው ገነት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛ ተርባይን ሃይል ማመንጨት መጀመሩን አስመልክተው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ የህዳሴ ግድብ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ከድህነት መውጫ መንገድ ተደርጎ የሚወሰድ ነው::

ድህነትን ማሸንፍና መልማት ዓለም አቀፋዊ መብት እንደሆነና ኢትዮጵያ ይህንን መብቷን በዓለም አቀፍ ህግ መሠረት ተጠቅማ የራሷን ሀብት እያለማች ያለች አገር መሆኗን የጠቀሱት ለዳት ፕሮፌሰሩ፤ ኢትዮጵያ በራሷ የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም የምታደርገው ጥረትም ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ተምሳሌት እንደሚሆንም አመላክተዋል::

የህዳሴ ግድብ አሁን ያለበት ሁኔታ ከምንም በላይ የታችኞቹን ተፋሰስ አገራት በማይጎዳ መልኩ ሦስቱ አገራት በመረጡት ገልለተኛ የኤክስፐርት ቡድን ተጠንቶ ሙሌቱ እየተከነወነ ይገኛል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ይህም ኢትዮጵያ የራሷን ሀብት በራሷ ማልማት



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

ረዳት ፕሮፌሰር ያየው ገነት

የምትችልና ራሷን ለመቻል እየሰራች ያለች አገር መሆኗን የሚያሳይ ነው ብለዋል::

ረዳት ፕሮፌሰር ያየው እንደተናገሩት፤ ግድቡ ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘርፈ ብዙ የሆኑ የልማት ችግሮች የሚፈቱበት ይሆናል:: ኢትዮጵያ በራሷ የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም የምታደርገው ጥረት ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ተምሳሌት እንደሆነም ተናግረዋል::

እንደ ረዳት ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ምንጊዜም ቢሆን ትብብርን መሠረት ያደረገ የልማት አማራጭን ተከትላ እየሄደች ትገኛለች:: የትኛውንም ትብብር ስትመርጥ የራሷን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፋ በመስጠት አይደለም:: የታችኛው ተፋሰስ አገራት ለረጅም ጊዜ ውሃውን በብቸኝነት ለመጠቀም ብዙ አይነት ስልቶችን ሲጠቀሙ ቆይተዋል:: ነገር ግን ኢትዮጵያ ሁሉም ነገር በሠላማዊና በትብብር እንዲደረግ አቋሟን ስታሳውቅ ቆይታለች:: የውሃ ሙሊቱም እየተካሄደ ያለው በዚሁ መንገድ ነው::

ሙሌቱን በተመለከተ ባለፈው ሳምንት ግብጽ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ያስገባቸው ደብዳቤ በሦስቱ አገራት የተፈረመውን የሦስትዮሽ የመርህ ስምምነት የጣሰ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳን ችግሮችን በራሳቸው ለመፍታትና የእርስ በእርስ መተማመን እንዲፈጠር ጉዳዩን በጋራ እንዲያዩ የተቀመጠ ስምምነት እንዳለ ጠቅሰዋል::

ችግሩ በስጋት ደረጃ እንኳን ቢኖር በአገራቱ መሪዎች ደረጃ ጉዳዩን ማየት እንዳለባቸው በስምምነቱ አንቀጽ 10 ላይ መቀመጡን ያወሱት ረዳት ፕሮፌሰር ያየህ፤ ነገር ግን ግብጽ ይህንን በተጻረረ መልኩ ደብዳቤውን ለተመድ ጽፋለች ብለዋል::

ጉዳዩ የልማት ጉዳይ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ሆኖም ግብጽ ብዙ ጊዜ የዓባይን ወንዝ የምትፈልገው የጸጥታ ጉዳይ አድርጋ እንደሆነ ተናግረዋል:: ነገር ግን ውሃው የደህንነት ችግር እንደሌለው በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች መረጋገጡን፤ ከዚህ አንጻር ግብጽ ምንም ችግር እንደማይደርስባት እየታወቀ ከኔ ውጭ ሌሎች ተፋሰስ አገራት መጠቀም የለባቸውም በማለት ጉዳዩን የጸጥታ ጉዳይ በማድረግ ላይ ትገኛለች ብለዋል::

የግድቡ ጉዳይ የብሄራዊ ጥቅም ጉዳይ ነው በማለት የኢትዮጵያ መንግሥት እያለመው ባለው የተፈጥሮ ሀብት ሥራው መቀጠል እንዳለበትም ገልጸዋል:: ከዓለም አቀፍ ሕግም ሆነ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም አንጻር እንዲሁም ድህነትን ለመቀነስና ልማትን ለማምጣት ሲባል ይህ ለኢትዮጵያ ትልቁ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል::

ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ "የኢትዮጵያ ድህነት በውርስ የሚቀጥል መሆን የለበትም:: ኢትዮጵያ ሕዝቦቿን በማስተባበር ያላትን ሀብት መጠቀም አለባት" በማለት፤ የህዳሴ ግድብ እየተሰራ ያለው የ2063 የዘላቂ ልማት ግብን ለማሳካት እንደሆነ መታሰብ እንዳለበትም ጠቁመዋል:: እውነታውን ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ለማስገንዘብ በሃይድሮ ዲፕሎማሲ ላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግም መክረዋል::

## "አሸናፊ ወጣቶች ወደ ዋናው ቡድን የሚገቡበት መንገድ ሊመቻች ይገባል"

**- ፍቅር ይልቃል**
**የስፖርት ጋዜጠኛ**

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ከወጣት የአትሌቲክስ ቡድኑ አሸናፊ የሆኑ ሯጮች ወደ ዋናው ቡድን የሚገቡበት መንገድ መመቻቸት አለበት ሲል የስፖርት ጋዜጠኛው ፍቅር ይልቃል ገለጸ:: ጋዜጠኛ ፍቅር ኢትዮጵያ በተከታታይ ላገኘቻቸው ድሎች ዋንኛው ምክንያት ከዚህ ቀደም የነበሩ ክፍተቶችን በመሙላት የተሰሩ ስራዎች ውጤት መሆናቸውንም አመልክቷል::

ጋዜጠኛ ፍቅር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ በኮሎምቢያ ካሊ ተሳትፎ ከአፍሪካ በአንደኝነት ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ ከሃያ ዓመት በታች የአትሌቲክስ ቡድን ላይ አሸናፊ ሯጮች ወደ ዋናው ብሄራዊ ቡድን የሚገቡበት መንገድ መመቻቸት አለበት::

ለብሄራዊ ቡድን በቂ የሆኑ አትሌቶች በጥንቃቄ ወደ ዋናው ቡድን እንዲመጡ ካልተደረገ ዘላቂ ውጤት ለማምጣት ይቸግራል ያለው ጋዜጠኛ ፍቅር፤ እንዴት ወደ ቡድኑ መሸጋገር ይችላሉ የሚለውን በመወያየትና የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ ስራዎች ሊሰሩ እንደሚገባቸውም ገልጿል::

በተከታታይ በተደረጉት ዓለምአቀፍ የሩጫ ውድድሮች በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ላይ ከፍተኛ ተስፋ ለማየት ችያለሁ ያለው ጋዜጠኛ ፍቅር፤ በኮሎምቢያው



የሃያ ዓመት በታች ውድድር የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በዘርፉ የነበረበትን ተተኪ የማፍራት ክፍተት የመሙላት ሂደት እንደነበረውም ነው የገለጸው::

ኢትዮጵያ የአትሌት ችግር የለባትም ያለው ጋዜጠኛ ፍቅር፤ ሥርዓት ባለው መንገድ የመመልመልና የመምራት ክፍተቶች ግን በተደጋጋሚ ሲስተዋሉ እንደነበር እንዲሁም ለአንድ ሀገር የሚሮጡ የማይመስሉ፣ የማይቀራረቡና የማይነጋገሩ ሯጮች እንዲሁም ከሯጮች የማይግባቡ አሰልጣኞች የነበሩበትን ሂደትም አስታውሷል::

በሩጫ ውድድሮች ላይ የሯጩ የግል ብቃት ከምንም ነገር በላይ አስፈላጊ መሆኑን የገለጸው ጋዜጠኛ ፍቅር፤ ከቁርጠኝነት፣ የመሮጥ ወኔና የግል ችሎታ ባሻገር በውስጣዊ አሰራር ላይ ያለ ሥነምግባርና የአሰራር ፍትሀዊነት ለተገኘው ድል ምክንያት ናቸው ብሏል::

የአትሌቶቹን ክፍተቶች ምንድናቸው ተብሎ የእያንዳንዱ አትሌት ድክመትና ጥንካሬ ላይ በመስራት ጥሩ ውጤት ማግኘት መቻሉን የገለጸው ጋዜጠኛ ፍቅር፤ ኢትዮጵያ በተከታታይ ላገኘቻቸው ድሎች ዋንኛው ምክንያት ከዚህ ቀደም የነበሩ ክፍተቶችን በመመሙላት የተሰሩ ስራዎች ናቸው ብሏል::

በሌሎች የስፖርት አይነቶች ላይ አሉ ለመባል ያህል እንዲሁም ለመርሀግብር ብቻ ሲሉ እንጂ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት ክፍተት እንዳለ የተናገረው ጋዜጠኛ ፍቅር ከሩጫው ትምህርት በመውሰድ ሊስተካከሉ ይገባቸዋል ሲል ነው የገለጸው::

በእግር ኳስ ላይ ያለው ለዘመናት የቆየ ችግር ባለው ችሎታ ልክ የሚመጥን ሥልጠና እንዲሁም አስተዳደር የመፍጠር ጉድለት መሆኑን የገለጸው ጋዜጠኛ ፍቅር፤ ያንን ክፍተት በመሙላትና ውስብስብ ችግሮችን በመፍታት በአትሌቲክስ ዘርፍ ላይ የታየውን አይነት ድል የሚጎናጸፍበትን መንገድ መፈለግ እንደሚያሻም ጠቁሟል::

## የግድቡ ኃይል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለዚህ ልዩ አገራዊ ስኬት መላው ሕዝባችንን እንኳን ደስ አላችሁ እያልን የህዳሴው ግድብ ለኢትዮጵያ፣ ለግብፅ፣ ለሱዳን እና ለአፍሪካ አህጉር በሙሉ ጠቃሚ መሆኑን አሁንም እናረጋግጣለን ብሏል።

እንደ አልአሩሲ ገለጻ፤ የህዳሴውን ግድብ ጥቅም ሁሉም በአይኑ ማየት ችሏል። ጉዳቱን እያዩ ያሉት የኢትዮጵያን እድገት እና ህዳሴን የተቃወሙ እና የጠሉ አካላት ብቻ ናቸው፡፡ የግድቡ ግንባታ ለማንኛውም አካል ጠቀሜታ እንጂ ጉዳት የለውም ሲልም ተናግሯል፡፡

ግድቡ አገራችንንና ሕዝባችንን ከችግር፣ ከመከራና ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቅልናል ያለው አልአሩሲ፤ ለመላ ኢትዮጵያውያን ጊዜያችሁን ሁሉ በደስታና በሠላም ይባርክ ሲልም የተሰማውን ጥልቅ ደስታ ገልጿል፡፡

የግድቡ 3ኛው ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቅ ኢትዮጵያ ግንባታውን አትጨርስም ለሚሉ ወገኖች ምላሽ የሰጠ ነው ያለው ሙሐመድ አልአሩሲ፤ የግድቡ 3ኛ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁ የመላው ኢትዮጵያውያን የጋራ ጥረት ውጤት ማሳያ እና የትብብር ውጤት መሆኑንም አመልክቷል፡፡

ግድቡ ከኢትዮጵያ በተጨማሪ የተፋሰሱን አገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ያብራራው አልአሩሲ፣ ከግንባታ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ በጋራ የመልማት እንጂ የተፋሰሱን አገራት የመጉዳት ፍላጎት እንደሌላት በተደጋጋሚ ማሳወቋን አውስቷል፡፡ መላ ኢትዮጵያውያን በቀጣይም በአንድነት በመቆም ብሄራዊ ጥቅማቸውን እንዲያስከብሩም ጥሪውን አስተላልፏል፡፡

## "በስፖርቱና በዓባይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የተገኘው ድልም እንደ ሀገር በቀጣይ የተሻሉ ስኬቶችን ለማስመዝገብ የሚረዳ ስንቅ ነው።

እንደ አሰልጣኝ ሰውነት ከሆነ፤ በስፖርቱና በግድቡ የተገኘው ውጤት ኢትዮጵያ በዓለምአቀፉ ማሕበረሰብ ዘንድ ያላትን ያልተገባ ምስል በመቀየር በቀና መንገድ እንድትተዋወቅ የሚረዳ ነው። ኢትዮጵያም በልጆቿ አማካኝነት ሰንደቋን በዓለም መድረክና በየመገናኛ ብዙሃኑ የምታስጠራበት መንገድ ተከፍቷል።

ልክ እንደአትሌቲክሱና እንደ ህዳሴው ግድብ ውጤት ማምጣት የሚችሉ በርካታ ሥራዎች ያስፈልጉናል ያሉት አሰልጣኝ ሰውነት፤ ድሎቹ በጎ ምግባሮችን እያስቀጠልን መጥፎዎቹን የምናስቀርበትን ትምህርት የሚሰጡ ናቸው ብለዋል።

በአንድ በኩል የዓባይ ግድብ ከመብራት በላይ ጥልቅ የሆነ ጥቅም አለው ያሉት አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው፤ በሁሉም መስክ ብዙ ሊጠቅም የሚችል ትልቅ ተቋም መሆኑን በመግለጽ ዘርፉን አስተባብሮና አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋልም ሲሉ ነው የገለጹት፡፡

በየዘርፎቹ የተገኙትን ድሎች በተለያዩ መስኮች መድገም እንደሚገባ ያመላከቱት አሰልጣኝ ሰውነት፤ በተለይም በተፈጥሮ ጥበቃ፣ ማሕበረሰብ አቀፍ ሥራዎችንና ትውልድ መቅረጽ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት በማድረግ እንደ ሀገር የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ ታዳጊ ሕፃናትንም በመንከባከብና ኮትኩቶ በማሳደግ አገር በቀጣይነት ያለው ድል እንድታስመዘግብ ጥረት ማድርግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በ19 አትሌቶች በሁለቱም ፆታ በ10 የውድድር ተግባራት ብቻ የተሳተፈው የአትሌቲክስ ቡድን በድምሩ በ12 ሜዳልያዎች ከዓለም ሀገራት ሶስተኛ ደረጃን ይዛ አጠናቃለች። በሌላ በኩል ሰሞኑን የህዳሴ ግድብ የሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት ከመጀመሩ ባለፈ የግድቡ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁ የሚታወስ ነው።

## ባለፋት አራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መመለስ መቻሉ የአረንጓዴ አሻራው ውጤት ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በመሆኑም ህዝቡ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሮች ላይ እያደረገ የሚገኘውን የችግኝ ተከላና እንክብካቤ ተግባር እንዲያጠናክር ጠይቀዋል።

በሐረሪ ያለው የሰላም የፍቅርና በአብሮነት የመኖር እሴት ማጠናከር እና ወደ ሌሎች አካባቢዎች ማስፋፋት ይገባል ብለዋል።

ሐረሪ አገራዊና ክልላዊ ልምድና ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት በክልሉ እየተካሄደ የሚገኘው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከፍተኛ ለውጥና እድገት ተመዝግቧል ብለዋል። እንደ ዋልታ ዘገባ፤ በአረንገዴ አሻራ የተመዘገበው ስኬት በሌሎች የሰላም፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዘርፎች ለመድገም ሕዝባችንን ባሳተፈ መልኩ በቅንጅትና በቁርጠኝንት ይሰራል ብለዋል።

ሐረር የፍቅር እና የሰላም መገኛ ነች። የዚህ ዓመት አረንገጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በሚጠናቀቅበት ምሽት፣ ተፈጥሮ የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄያችንን ውጤት በገለጠችበት ሥፍራ አሻራችንን አሳርፈናል ሲሉ ስለትናንትናው መርሃግብር በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው አስፍረዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይም ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፣ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ፣ የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪና ሌሎች የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም የአገር ሽማግሌዎችና አባገዳዎችም ተገኝተዋል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ከእንጨት መርጦ ለታቦት ፤ ከሰውስ?

ግርማ መንግሥቴ

ከእንጨት መርጦ ለታቦት ... እንዲሉ ፈጣሪም ከሰው መርጦ ለሰው ሰው ይሰጣል፤ ለሹመትም እንደዛው።

ለራሱ ሳይሆን ለሰው የሚሆን እንዳለ ሁሉ፤ ለራሱ ብቻ የሚኖረው ቁጥሩ ይበዛል። አያድርስ እንጂ ለራሱም ለሰውም ሳይሆነው ሁሉም የሚያልፍበትም አለ። ለራሱም፣ ለሰውም ሆኖ የሚኖረውም ሆነ የሚያልፈው ደግሞ ቁጥሩ እጅግ ትንሽ ነው እንጂ አለ። የዚህ ሚስጥሩ ምንድን ነው? ከዛሬው የአምዳችን እንግዳ የምንሰማው ይኖራል።

በጓደኞቻቸው፣ ባልደረቦቻቸውና አካባቢያቸው ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው፣ በስራ ህይወታቸው ... አልችልምን፣ አቃተኝ፣ ታከተኝን፣ ደከመኝ ...ን ባለማወቃቸው "ዶዘር"፤ በልፋት፣ ጥረታቸውና በሚያገኙት ስኬት ምክንያት በኦሮምኛ "ሮሬሳ" (ጀግና)፤ ነገሮችን ባለመርሳት፣ እያንዳንዱን በማስታወሳቸው ... "የኢትዮጵያ መዝገብ" የሚሉ የተለያዩ ቅፅል መጠሪያዎችን ያተረፉት የዛሬው እንግዳችን ለአገራቸው ብዙ ለፍተዋል። ለሚኖሩበት አካባቢ ማህበረሰብ አገልግለዋል፤ ላፈራቸው ህብረተሰብ ከሚችሉት ርቀት በላይ በመሄድ ሰርተዋል፤ አገራቸውን በመወከል አገራትን አካልለዋል ...። እንዴትና ለምን የሚለውን እራሳቸው፣ ከአንባቢ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነትን በመፍጠር "እኔ" እያሉ፤ ይነግሩናልና በቆይታችን የምንደርስበት ይሆናል።

ሶስት የአገር ውስጥ (ከእንግሊዝኛው ጋር አራት) ቋንቋዎችን እያገላበጡ የሚጠቀሙት የዛሬው እንግዳችን የአስተዳደር ዓለም ሰው ናቸው፤ የድርሰት ዓለም ሰው ናቸው፤ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪም ናቸው። የተሳካለት ባለትዳር ብቻ ሳይሆኑ የሁለት የአካዳሚው ዓለም ጀግኖች፤ በአንድ ወቅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ "ሁለቱ ከዋክፐት ወንድማማቾች" (እንግዳችን እንደ ነገሩን) በማለት የዘገበላቸው ልጆች አባትም ናቸው። ፓርላማና ቤተ መንግስቱንም ተመላልሰውበታል። ምን ቀረ፣ የቀረውን ራሳቸው አቶ ተስፋዬ ጎይቴ ይነግሩናልና እንሰማቸዋለን።

የዛሬው እንግዳችን መንግስታትን በቅርበት የሚያውቁ፤ በደርግ ተምረው የስራውን ዓለም የተቀላቀሉ፤ በኢህአዴግ በየዘርፉ እየሄዱና እየተወሰዱ ያገለገሉ፤ በአሁኑ ብልፅግናም በተለያዩ ኃላፊነቶች ከመስራትም ባለፈ በአማካሪነት በመስራት ላይ የሚገኙ፤ ቆፍጣና ሲሆኑ፣ በየስርአቶቹ ምን ታዘቡ? ይህንንም የምንሰማቸው ይሆናል። ከትውልድና እድገታቸውም ይጀምሩልናል።

### ትውልድና እድገት

በ1952 ኢ.ም ተወልጄ ያደግኩት በአምቦ መንገድ፣ አዲስ አበባ ዙሪያ፣ በወልመራ ወረዳ፣ ከመዲናዋ 37 ኪ/ሜ ላይ በምትገኘው ሆለታ አካባቢ ነው። ማህበረሰቡ ለረጅም ጊዜ አብሮ ከመኖሩ የተነሳ ቋንቋዎቹን ተወራርሷል። እኔም አማርኛ፣ ጉራጊኛና ኦሮምኛን እየተናገርኩ ነው ያደግኩት። አባቴ ከአገር ቤት ወደ ሆለታ መጥቶ ነው ነዋሪ ሊሆኑ የቻለው።

የስራ መሳሪያው የሆነውን ከባዱንና ባለ ሁለት እግሩን የጉራጌ የብረት ማረሻ በአንድ ትከሻው፣ ለመንገድ ቀለብ የሚሆነውን የቆጮ ስንቅ በአናቱ ተሸክሞ ነው ከትውልድ አካባቢው ከምድረ ጉራጌ ተነስቶ አውሬዎችን ሳይፈራ ቀንና ሌሊት በእግሩ ተጉዞ ዋቤ ወንዝን በሀረግ ድልድይ ተሻግሮ (ያኔ ድልድዮች ስላልነበሩ)፤ በቱሉቦሎ አቆራርጦ ሆለታ ከሚባል አገር በአራት ወይም በአምስት ቀኑ ይደርስ የነበረው። ይሄ የሁሉም ቀደምት ጉራጌዎች ጣፋጭ ታሪክ ነው። ጥንካሬውም ከዚህ ይጀምራል።

አባቴ በቀን 10 ሳንቲም፣ ከቀናውም ስሙኒ ወይም ሽልንግ የጉልበት ክፍያ እየተከፈለው ነበር እዳሪ መሬቶችን በማረሻ የሚደቀድቀው። ገንዘቡ ትንሽ ጠርቀም ሲልለት አገር ቤት ቤተሰቦቹን ተመላልሶ ይጠይቅ ነበር። ኑሮውን ብቻውን መግፋት ሲሳነው ቤተሰቦቹን ከአገር ቤት ወደ ሆለታ አመጣ። ደሀ ገበሬ ነበርና ያቅሙን ጎጆ ቀልሶ ከእናቴ ጋር በጋራ ኑሮአቸውን መግፋት ጀመሩ። ከዚያም እኔ 6ኛው ልጃቸው ተወለድኩ፤ በሆለታ ምድር። በጠቅላላው 10 ልጆችን አፍርተዋል።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያናችን አስተዳዳሪ የነበሩት የክርስትና አባቴ እጅግ ይወዱኝ ነበር። በሰፈራችን በሚገኘው የቄስ ትምህርት ቤት በልጅነቴ ትምህርቴን እንድጀምር ከዚያም በቤተክርስቲያኒቱ እያገለገልኩ እንዳድግ ተደረገ። ወላጆቼንም በአንዳንድ ስራዎች እያገዝኩ ማለት ነው። ያኔ የሆነ ጥፋት አጥፍተን የአካባቢያችን ሰዎች ቢያገኙን ድብን አድርገው ይቆነጥጡናል። ይገርፉናል። መጥፎ ባህሪ እንዳናዳብር ሁሉም ሰው ይከላከል ነበር። ልጁን ብገርፍበት እገሌ ይቀየመኛል የሚል የተዛባ አስተሳሰብ በፍጹም አልነበረም። የመልካም ስነምግባርና መልካም ሰብእና ባለቤትነቱ እንግዲህ ከዛ ይጀምራል ማለት ነው።

### የትምህርት ቤት ሕይወቴ

የ1ኛ ደረጃ ትምህርቴን በአባ ወልደማርያም እና በወልመራ ፊላንድ ሚሲዮን፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቴን በደጃጅዝማች መንገሻ ይልማ (በኋላ ሆለታ አጠቃላይ) ትምህርት ቤቶች ነው የተማርኩት። አንዳንድ መሰናክሎች በገጠሙኝ ጊዜ ካልሆነ በስተቀረ ውጤቴ በየአመቱ በጣም የሚያረካ ነበር። በአጠቃላይ ከ1ኛ - 3ኛ የመውጣት ታሪክ ነው ያለኝ። እንዲያውም "ደብል" በሚባለው በአንድ አመት ሁለት ክፍሎችን የማጠናቀቅ ስርአት፣ 3ኛ እና 4ኛ ክፍልን በ1 ዓመት ነው የተማርኩት። 6ኛ እና 8ኛ ክፍልንም በ1ኛነት ነው ያጠናቀኩት። ከ9ኛ - 12ኛ ግን ውጤቴ አጥጋቢ አልነበረም። የታዳጊ ነገር ሆኖ ወደ ፖለቲካው አዘንብዬ ለትምህርቴ ብዙ ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር።

በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት በኢህአፓ አባልነት ተመልምዬ እያገለገልኩ እያደር ፓርቲውን በፍቅር ወደድኩት። አብዛኛውን ጊዜዬንም ሰዋሁለት። ፕሮግራሙን፣ ልሳኑን፣ ልዩ ልዩ ሰነዶቹን ማንበብ፣ ማጥናት፣ ወረቀት መበተን፤ መረጃዎችን በየእንስቱ፣ ጭዱ፣ ኮባው ... ውስጥ መደበቅ ሆነ። በዚህም ጸረ አብዮተኛ ተብለን ከጓደኞቼ ጋር ሁለት ጊዜ እስር ቤት ተከረቸምን። ማትሪክ ፈተና ከእስር ቤት በፖሊስ ታጅበን እየተመላለስን ተፈተንን። እንዳንጠፋ (እንዳናመልጥ) በፊት ለፊታችን ጠመንጃ ተደግኖ ነበር የተፈተንነው።

ለማንኛውም የኔ ከመላ አገሪቱ የአካዳሚክ ጉልበት ያላቸው ምርጥ ተማሪዎች ይማሩበት ወደነበረው የዊንጌት ትምህርት ቤት ለመግባት ፈተናውን አልፌ ት/ቤቱ ፕሮግራሙን በመቀየሩ ምክንያት ነው እድሉን ያላገኘሁት። ይህም ሆኖ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርቴን ተከታትዬ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመረቅሁ (1979 ኢ.ም)፡ የተሻለ ውጤት ከነበራቸው ተማሪዎች አንዱ ስለነበርኩ ዲግሪዬን የተቀበልኩት ከወቅቱ ፕሬዝደንት መንግስቱ ኃ/ማርያም እጅ ነው። ከዚያ በኋላ በስራ ዓለም እያለሁ እጅግ በርካታ የአመራር አቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በአገር ውስጥም በውጭም ተከታትያለሁ። ስልጠናዎቹን እጅግ በጣም እንደተጠቀምኩባቸው እረዳለሁ። በዚህ አጋጣሚ ከታች እስከ ላይ ያስተማሩኝን መምህር በረዳው፣ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ፣ ዶ/ር አለማየሁ አዘዘ፣ ረ/ፕ ዘሪሁን አስፋው ... ሌሎችንም ማመስገን እፈልጋለሁ።

### የስራ ሕይወቴና አገራዊ አስተዋጽኦዬ

"ሀ" ብዬ ስራ የጀመርኩት በአ/አ ቄራዎች ድርጅት ነው፤ የህዝብ ግንኙነት ሰራተኛ ሆኜ። በ1.8 ዓመት ቆይታዬ በአ/አ ከተማ ነዋሪዎች የስጋ ፍጆታ፣ ዘመናዊ ኢንዱስትሪያል ቄራ በሚገነባበት የቦታ ጥናት በትጋት ተሳትፌያለሁ። የ "ዜና ቄራ" መጽሄት 1 እትም ዋና አዘጋጅ ነበርኩ። ማኔጅመንቱ፣ የሰራተኛ ማህበሩ እና የፓርቲ ጽ/ቤቱ ጭምር በአጭር ጊዜ ባሳየሁት ውጤት እጅግ ስለተደሰቱ በሶስት ወር ነው የደመወዝ ጭማሪ የተደረገልኝ።

የአገሪቱ አጻደ ምሁራን ይባል ከነበረው "የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት" ትፈለጋህ ተብዬ ተጠራሁ። ባልተቋረጠ የሚዲያ ተሳትፎዬ ያውቁኝ ስለነበረ ይመስለኛል። 2ኛ ዲግሪ ከነበራቸው ጋር ተወዳድሬ በተሻለ ውጤት ተመረጥኩ። በህዝብ ግንኙነት ባለሙያነትም ተቀጠርኩ። በየደረጃው የአቅሜን ሰራሁ። እድገቶችንም አገኘሁ። በ "የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት" ውስጥ ከሚሰሩ ስመጥር ምሁራኑ የተማርኩት እስከ ዛሬም ስንቅ ሆኖኛል። መማር፣ መማር .... ተጨባጭ ውጤት ማሳየት።

ያኔ በቃለ-ጉባኤ አያያዝ ፍጥነትና ጥራት የሚስተካከለኝ አልነበረም። ምሁራኑ የሕገ-መንግሥት፣ የብሔረሰቦች ታሪክ፣ ቋንቋና ባህል ጥናትና ውይይት ሲያካሂዱ ቃለ-ጉባኤ መዝጋቢ እኔ ነበርኩ። በአስተዳደርና ራስ ገዝ አካባቢዎች ጥናት ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው በአቅሜ ሰፊ ተሳትፎ ነበረኝ። ቆይቶም በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ (ኢህዲሪ) ምርጫ ኮሚሽን፣ በብሄራዊ ሸንጎ፣ በመንግስት ምክር ቤት በቃለ-ጉባኤ ያዥነት ተመድቤ የአገሪቱን ብርቱ ብርቱ ሚስጥሮች ጠብቄ ሰርቻለሁ። ለአገሪቱ መረጃዎች ቅርብ ነበርኩ። የብሄራዊ ሸንጎን ውሳኔዎች ለማስተዋወቅ፣ የምርጫ ክልሎችን ለማደራጀት፣ በወያኔ የአጸፋ ፕሮፓጋንዳ ግብረሀይል ስራ መላ አገሪቱን የመዘዋወር እድል አግኝቻለሁ። የምክትል ፕሬዝደንቱ ልዩ ረዳት ሆኜም ለተወሰነ ጊዜ ሰርቻለሁ።

ኢህአዲግ ስልጣን እንደተቆናጠጠ የነበረኝን ልምድ፣ የስራ ተነሳሽነትና ተደራራቢ ስራዎችን የማሸነፍ አቅሜን በማገናዘብ በምርጫ ኮሚሽን ጽ/ቤት አስተባባሪነት ተደራቢ ኃላፊነት ሰጠኝ። በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት (አሉ የተባሉ ምሁራን የተሰባሰቡበት፣ የዛ ተቋም መፍረስ በጣም የሚቆጭ ነው) የትምህርትና ማስታወቂያ መምሪያ ኃላፊም ሆኜ ተመደብኩ። በተለይ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ የነበሩት አመታት በታሪኬ ውስጥ ካለፉት አመታት በበለጠ ለአገሬ የጎላ አስተዋጽኦ ያደረኩበት ወቅት ይመስለኛል። በአንድ የወር ደመወዝ በርካታ ኃላፊነቶችን ደርቤ መወጣቴ ነበር የተለየ የሚያደርገኝ።

በሽግግሩ አመታት ልዩ ልዩ ፈተናዎችን ተቋቁመን ጊዜያዊ ምርጫ አካሄድን። በአብዛኛዎቹ ክልሎች ምስረታ ላይ አስተባባሪና የበላይ አካልን በመወከል ከቡድኖቹ ጋራ በየጉባኤዎቹ ተገኝቻለሁ። በተለይ የሱማሌ ክልል ምስረታ የተለየና ለአደጋም ያጋለጠኝ ነበር። በዚች አገር ጀምበር ስር ከተሳተፍኩባቸው ትልልቅ አገራዊ ጉዳዮች የሚጠቀሰው በክልሎች መካከል የተፈጠሩትን ያለመግባባቶች ለመፍታት ያደረኩት ጥረት ነው። በተካሄዱት ድርድሮች በገለልተኛ ታዛቢነት፣ በአስተባባሪነት፣ በኋላም በገለልተኛ ዋና አደራዳሪነት አገሬ የሰጠችኝን አደራ ተወጥቻለሁ። ሰላም እንዳይደፈርስ፣ አጎራባች ህዝቦች በፍቅር እንዲኖሩ በሕይወት ላይ ዋጋ መክፈልን የሚጠይቅ ተልእኮ ነው የተወጣሁት።

ተደራራቢ ስራዎች ሲሰጡኝ አለቆቼ "ስለምንተማመንብህ ነው" ይሉኝ ነበር። በተለይ ኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን ለማቋቋም የተሰጠኝ ተደራራቢ ተልእኮ ሰፊ ነበር። የቦርዱ ያደረጃጀት፣ የሰው ኃይልና የበጀት ጥናት ግብረ ኃይል ሰብሳቢ ሆኜ በተጨማሪ የሌሎች ግብረ ኃይሎች ጥናቶችን አግዝ ነበር። አምስት ትልልቅ ጥናቶች በግብረ ኃይል ሲጠናቀቁ የጥናቶቹ አጣጣሚ ልዩ ግብረ ኃይል ሰብሳቢ ሆኜ ተልእኮዬን በብቃት ተወጥቻለሁ። በስዊድን ባለሙያዎች እየታገዝኩ።

የሕገ መንግስት ኮሚሽን ተቋቁሞ ያደረጃጀትና አሰራር ዝርጋታ እንዳግዝ ተጠይቄ በሙሉ ፈቃደኝነት ሰርቻለሁ። "በአንድ ሰው ደመወዝ ይሄን ሁሉ ስራ?" የሚሉኝም ብዙ ነበሩ። ቅዳሜ እና እሁድ፣ በበዓል ቀናት፣ ምሽቱን ሁሉ እንሰራለን። ይህ ሁሉ የመንፈስ ልእልና፣ ለህዝብ ተቆርቋሪነት፣ አገር ወዳድነት የፈጠረው የኃላፊነት መንፈስ ነው። ይህ፣ የነገው አገር ተረካቢው ወጣት (ነገ የእሱ ነውና) ከዚህ በትልቁ መማር አለበት፤ ፖለቲካ ፋሽን ነውና ፋሽኑን የተከተለ ተቃውሞ እንጂ እንደ ድሮው ድንጋይ መወርወርን መድገም የለበትም። በአንድ ቀን 400 ሱቆች ተቃጥለዋል፤ ለምን? ከሚል እንጂ በቀብሬ ላይ የሚነበብ የሕይወት ታሪኬ አይደለም።

በመጨረሻ የምርጫ ቦርድ አባላትንና የጽ/ቤቱን የበላይ ኃላፊዎች በቻርተሩና በምርጫ ህጉ መሰረት ለመሾም በ1985 ዓ.ም መጨረሻ በተካሄደው የእጩዎች ምልመላ እኔ በጉልህ አስተዋጽኦዬ የተነሳ በመሰረትኩት ተቋም ለም/ዋና ኃላፊነት ታጭቼ በ1986 ዓ.ም መጀመሪያ በሽግግሩ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት ሹመቴ በፓርላማ ጸድቆ ስራ ጀመርኩ። ታዲያ በትምህርት ደረጃቸው፣ በሙያ ዝግጅታቸው፣ በረጅም አገልግሎታቸው እጅጉን የሚኮፈሱ ባልደረቦች ቦታው ለእኛ ይገባ ነበር በማለት ቅሬታ ሳያቀርቡም አልቀሩም። በወሬ ሳይሆን በተግባራዊ ውጤታችን ግን አንደራረስም ነበር።

በወቅቱ በዚህ የም/ሚኒስትር ደረጃ (ማእረግ) በነበረው ከፍተኛ ኃላፊነት ለስድስት ዓመታት ያህል



ፎቶ : በፀሐይ ንጉሴ

አቶ ተስፋዬ ጎይቴ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

በፍጹም ታማኝነትና ቅንነት የምወዳትን አገሬንና ከልቤ የምቆረቆርለትን፣ በምንም አይነት የግል ፍላጎቴንና ጥቅሜን የማላስቀድምበትን የኢትዮጵያ ህዝብ አገልግያለሁ። በሁሉም ኃላፊነቶቼ ውስጥ ከሹመኝነት ይልቅ ባለሙያነት እያዘነበለብኝ ከባልደረቦቼ ጋር በቡድን ተልእኮአችንን ተወጥተናል። ገና ጸረ ሙስና ኮሚሽንና እንባ ጠባቂ ሳይፈጠሩ በምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ውስጥ የነበረውን የገነነ ሙስናና ብልሹ አሰራር ከባልደረቦቼ ጋር በሚዲያና በየመድረኩ ከጅምሩ ጀምሮ በማጋለጥ ታግለናል። የተቋሙ መልካም ገጽታ እንዳይጠለሽ አብዝተን ጥረናል። በ1987 ዓ.ም የተካሄደውን የመጀመሪያውን አገራዊ ምርጫ መርተናል። በ1992 ዓ.ም ለሚካሄደው 2ኛ ምርጫ ዝግጅት ጀምረን ነው በ1991 ዓ.ም መገባደጃ ችግር የገጠመን።

በቦርዱ ውስጥ የሰፈነውን ብልሹ አሰራር ለተከበረው ፓርላማ መደበኛ ጉባኤ በአካል ቀርቤ ንግግር በማድረግ ግልፅልፅ አድርጌ አጋለጥኩ። ባለስልጣን ሆኜ በባለስልጣናት የሚካሄደውን ሙስና በማጋለጤ የተከበሩት የምክር ቤቱ አባላት አዳራሹን ከዳር እስከ ዳር በረጅም ጭብጨባ አቀለጡት። ወዲያውኑ የአገሪቱ ሚዲያዎች ዜናውን ተቀባብለው አስተጋቡት። “ፓርላማው ፓርላማ ሆኖ ዋለ” የሚል ሰፊ ዜና ናኘ። የአድናቆት ጋጋታ አስተጋባ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ምክር ቤቱ በሌላ ስብሰባው ውሳኔውን እንዲቀይር ተደርጎ ነገሩ እውነት ቢሆንም በገሀድ ማጋለጥ አልነበረበትም ተብሎ ከኃላፊነቴ እንድነሳ ተወሰነ። ለሁሉም አስደንጋጭ ክስተት ነበር። ሚዲያዎች ተመልሰው “ተስፋዬን ያየህ ተቀጣ” የሚል ዜና አስተጋቡ። በውሳኔውም ተሳለቁ። ጓዜን ጠቅልዬ ከተቋሙ ወጣሁ። ትልቅ ግፍ ነበር የተሰራው።

“ቸር ኢትዮጵያ” የሚባል የበጎ አድራጎት ድርጅት ቀጠረኝ። ለአራት ወራት ያክል እንደሰራሁ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተጠርቼ ወደ መንግስት ቤት እንድመለስ ተነገረኝ። ወዲያው በከተማ ልማት ሚኒስቴር በብሄራዊ ከተሞች ጥናት ኢንስቲትዩት የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ ኃላፊ ሆኜ ተመደብኩ። ከትምህርት ዝግጅቴ ውጭ። ስራዬን ግን በፍቅር ቀጠልኩ። አልተሸነፍኩለትም። የሚገርመው ነገር አሁንም ለተወሰነ ጊዜ የህዝብ ግንኙነት አገልግሎት እና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ኃላፊ መደቦችን ደርቤ አገልግያለሁ። የኢትዮጵያ ከተሞች የልምድ ልውውጥ አስተባባሪ ኮሚቴ አባልና ጸሀፊም ነበርኩ። “ከበደኝ” ብዬ አላውቅም። ከተቋሙ ስለቅ አለቃዬ “ትከሻዬ ተገነጠለ” ነበር ያሉት። ሶስት ዓመት ተኩል ነው ያገለገልኩት።

በኢትዮጵያ ማህበራዊ ኢንሹራንስ በደንበኞችና ፋሲሊቲ ኃላፊ የማኔጅመንት መደብ ተወዳድሬ አለፍኩ። ዋው!! በጣም በመግባባት ህያው ስራ የሰራንበት መስሪያ ቤት ነው። ማኔጅመንቱ ውስጥ ተሳትፎዬ ሰፊ ነበር። የቦርዱ ጸሐፊም ነበርኩ። ባቀረብኩት መነሻ ሀሳብ መሰረት የኢትዮጵያ ማህበራዊ ተቋማትን ለማብቃት አገር አቀፍ የትብብር ፎረም ተቋቋመ። የፎረሙ አስተባባሪ ነበርኩ። ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በየክልሉ ዞረን አማክረን ነው ፎረሙ የተቋቋመው። በነበረኝ ተሞክሮ ሁለት ባልደረቦቼን ይዤ የአማራ ማህበራዊ ኢንሹራንስ ለማገዝ ሄድን። በቢፒአር ጥናትና ትግበራም ሰፊ ተሳትፎ ነበረኝ። አቅሜ እያደር እያደገ ሄደ።

ያኔም ለረጅም ጊዜ (እሁድ ሳይቀር) ቢፒአር ስራ ላይ ተጠምደን እንውል ነበር። አዳዲስ ሀሳቦችን እያመነጨን ነበር ስንሰራ የነበረው።

የደብረ ዘይት ስራ አመራር ማሰልጠኛን በመሰረታዊነት ለማሻሻል የተቋቋመውን ግበረሀይል በሰብሳቢነት መራሁ። የተቋሙ የአደረጃጀት ጥናት ሲጠናቀቅ አስተዋጽኦዬ ታሳቢ ሆኖ የፋሲሊቲና ሰርቪስ አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ ሆኜ ተመደብኩ። የደብረ ዘይት ስራ አመራር ማሰልጠኛ ማእከል ተጠሪነት ለዚህ ትልቅ ዘርፍ ነበር። ያኔ በጋራ ሆነን በ“ይቻላል” መንፈስ ያልሞከርነው የለም፤ አልተሸነፍንምም። ከመስከረም 1 ቀን 1996 – መጋቢት 1999 ካገለገልኩበት ኢትዮጵያ ማህበራዊ ኢንሹራንስ በሹመት ወደ እምባ ጠባቂ ተቋም ተመደብኩ።

መጀመሪያ በፕላንና ዓለም አቀፍ ትብብር ኃላፊነት በኋላም ወደ መልካም አስተዳደር መምሪያ ኃላፊነት



ተዛውሬ የአስተዳደር በደልን ለመከላከል የሚያግዙ ሰፋፊ መሰረቶችን ጥለናል። ከፓርላማው ጀምሮ ለሁሉም ክልሎች ስልጠና ሰጥተናል። በርካታ አወደ ጥናቶችንም አካሂደናል። ጥናቶችን አስጠንተናል። ለየአካላቱ እየዞርን ስልጠና ሰጠን። በዚያን ወቅትም የዲሞክራሲ ተቋማት በነጻነት ለብቻቸው ምንም ያህል ለውጥ ማምጣት ካልቻሉ ለምን አይዋሃዱም? የሚል ጥናት በአፈጉባኤው በተመራው የቢፒአር መድረክ ላይ በድፍረት አቀረብኩ። በሚዲያም ብዙ ስራ ሰራን።

የመረጃ ነጻነት አዋጅ ትግበራ ዝግጅት ግብረ ኃይል ተቋቋመ። የግብረ ኃይሉም አባልና ጸሐፊ ሆንኩ። የቴክኒክ ቡድን ተዋቅሮ የማስፈጸሚያ ረቂቅ ደንቦችና መመሪያዎች አዘጋጅተን በየደረጃውም ግንዛቤ ፈጠርን። ከቱባ ባለስልጣናት ጋር ነበር የምንሰራው። በውጭ ተሞክሮ እየታገዝን ነበር። ዘመኑ ዘመነ ቢፒአር (ቢዝነስ ፕሮሰሲንግ ኢንጂነሪንግ) ነበር። ግምባር ቀደም ተሳታፊ ነበርኩ። እስከ 2003 መጀመሪያ አገለገልኩ። 3/4ኛውን የስራ ዘመኔን ያሳለፍኩት በአመራርነት ነው። ዝርዝሩ ብዙ ነው።

### የስነ ጽሁፍ ሕይወቴ

ከሂሉ የ1ኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ ነው ቀልቤን የሰረቀው። ግጥም እየጻፍኩ በየክፍሉ እየተዘዋወርኩ አነብ ነበር። ለጓደኞቼ የፍቅር ደብዳቤ በግጥም የምፅፈው እኔ ነበርኩ። በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሰንደቅ አላማ ሲሰቀል ግጥም አቀርብ ነበር። በሬዲዮም ማቅረብ የጀመርኩት ያኔ ነው። ከ1970ዎቹ ጀምሮ በ“ዜና ቱሪዝም” ቋሚ ጽሁፍ አቅራቢ ሆንኩ። በለገዳዲ ሬዲዮም “ሃውልቱ ይናገር” የሚል ፕሮግራም ነበረኝ። የ5 አመት ሰርተፊኬት ተሸልሜያለሁ። አዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች ላይም እጽፍ ነበር። አዲስ ዘመን ያኔ “እንደፍታ ከወጣቱ ከያኒ ጋር” ብሎ አስተዋውቆኛል። በተለያዩ የስነጽሁፍ ውድድሮች ተሸላሚ ነበርኩ። ለከፍተኞች የኪነት ቡድኖች ግጥሞችን በአማርኛ፣ በጉራጌኛ፣ በኦሮምኛና በእንግሊዝኛ በልደት፣ በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት፣ አርሲና ሙገር አቀርብ ነበር።

ያኔ በጉራጌኛ አራት ያህል መጻሕፍት ብቻ ነበሩ የታተሙት። እነርሱን ሳነብ ለካንስ በጉራጌኛም መጻፍ ይቻላል ብዬ ሙከራ ጀመርኩ። ኦሮሚያ የተወለደው ተስፋዬ “የኬርጋት” የተባለውን የመጀመሪያውን የጉራጌኛ መጽሃፉን በ1993 ኢ.ም አሳትሞ ለአንባቢያን ጀባ አለ። የህትመት ወጪ እየተወደደም ቢሄድ በ2005 2ኛ መጽሃፌን “ግራጌንደ”ን አሳትሜ ለንባብ አበቃሁ። ይህ ሁሉ ሲሆን በአንዳንድ ወዳጆቼም ተደግፌ ነው። በ2006 3ኛው መጽሐፌን፣ “ስንክርተነ” ወጣ። ብዙ ጊዜ የሰጠሁትን የኢፌዴሪ ሕገመንግስት የጉራጌኛ ትርጉም በ2008 4ኛ ስራዬን አስገምግሜ “ቡር ቂጫ” በሚል ስያሜ አሳትሜ አበርክቻለሁ።

መጽሃፎቼ ጉራጌኛ ቋንቋን ለመታደግ እና ባህሉን ለማስተዋወቅ አግዘዋል። የአገር ችግሮችን ዳሰዋል። ዓለምንም ነካክተዋል። 5ኛው ስራዬ ተጠናቆ የህትመትን ጀንበር ይጠብቃል።

“የመረጃ ነጻነት በኢትዮጵያ”፣ “አዲስ አበባ” እና ሌሎች፣ ከተጠናቀቁ በጣም የቆዩ ስራዎቼ “ብርሃን አሳየን” ብለው እየተማፀኑኝ ይገኛሉ። አሁን ችግሩ የህትመት ዋጋ መናርና የአቅም ውስንነት መኖሩ ነው።

ኢትዮጵያን በሙሉ የሚሸፍን አንድ ትልቅና ጥልቅ ጥናትም እያጠናሁ ነው። መረጃዎችን ሰብስቤ ጨርሻለሁ። ጥናቱም የጉራጌኛ ስያሜ ያላቸውን የንግድ ተቋማት መለየት ሲሆን እስካሁን 2ሺህ በላይ አግኝቻለሁ። አላማውም የጉራጌ ብሄረሰብ ምን ያህል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ቦታ ለማሳየት፤ የጉራጌን ኢትዮጵያዊነትም ለመገንዘብ፤ ከስራ ጋር ያለውን የጠበቀ ትስስርም ለማሳየት ያግዛል። ሌሎች በርካታ ውስብስብ ጉዳዮችንም ያነሳል።

ጥቂት የካሴት ዘፈን ግጥሞችም አሉኝ። ከሃያ አመታት በላይ በዓለም የቱሪዝም ቀን፣ በኢትዮጵያ የባህል ሳምንት እና በመሳሰሉ ክብረ በአላት ላይ በሸራተን፣ እንዲሁም በሁሉም ክልሎች በዙር ሲከበር በመሪ ቃሉ ላይ ብቸኛ ግጥም አቅራቢ እኔ ነኝ። በርካታ የምስክር ወረቀቶችን ያገኘሁ ሲሆን፤ አንዱም ከሚኒስትር ቢልልኝ ማንደፍሮ እጅ የተቀበልኩት ነው።

ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ለአብያተ ክርስቲያናት ... መጽሄቶችን በነጻ አዘጋጅቻለሁ። በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በመረጃ ነጻነት ላይ 25 ተከታታይ አንቂና ግንዛቤ አስጨባጭ ጽሁፎችን በብዕር ስም አቅርቤያለሁ። ከ1980ዎቹ አጋማሽ በኋላ በተለያዩ መጽሄቶችና ጋዜጦች ላይ ለንባብ የበቁ በርካታ ወቅታዊና ታሪካዊ መጣጥፎች ነበሩኝ። እስካሁንም በሪፖርተር ጋዜጣ ትኩረት በሚሹ አገራዊ ጉዳዮች ላይ እጽፋለሁ። የምመክረውን እመክራለሁ፤ የምገስጸውን እገስጻለሁ። አንዳንዴም የትውልዱ አንዳንድ የተዛቡ አካሄዶች በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚያሳስቡኝ ሚዲያ ላይ ወጥቼ መሆን ያለበት እንዲሆን፤ መሆን የሌለበት እንዳይሆን አደራ እላለሁ።

### ሳፈራኝ ብሔረሰብ

የጉራጌ ብሔረሰብ ቋንቋውን፣ ባህሉን፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ሕይወቱን፤ ወግና ትውፊቱን ለማስተዋወቅ ሳልታክት ፅፌያለሁ። በየዓመቱ የጉራጌ መስቀልን ገጽታ በበርካታ ሚዲያዎች በስፋት ማስተዋወቅ ከጀመርኩ 20 አመታት አልፈውኛል። በ16 አመታት ተከታታይ ጥረት ከጓደኞቼ ጋር ከ100 በላይ አባላት ያሉት የጉራጌ የኪነጥበብ ባለሙያዎች የጋራ መድረክ አቋቁመን ነበር። ብዙ መቀጠል አልቻለም። የጉራጌ አንዱ አካል የሆነው የእዣ ክፍለ-ህዝብ ልማት ማህበር ሊቀመንበር ሆኜ ለስድስት ዓመታት ያህል አገልግያለሁ። ዛሬም ለአዲስ አበባ ከተማ ሞዴል ሆኖ እየወጣ ያለውን የእዣ እድሮች ህብረት በሙያዬ እያገዝኩ እገኛለሁ። ለጉራጌ ዞን ለማህበረሰቡ የልማትና የባህል አደረጃጀቶች በተጠየቅኩ ጊዜ ሁሉ አሻራዬን አኑሬአለሁ። ይህ የሚቀጥል ይሆናል።

ከጠቅላይ ሚኒስትር ጀምሮ እና ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች የተገኙባቸውን፣ ትልልቅ ሁነቶች የተከናወኑባቸውን የተለያዩ መድረኮች መርቻለሁ።

### ከትውልድ አካባቢዬ ጥሪ ደረሰኝ

ከመንግስት ቤት ወጥቼ የቤተ ጉራጌ ባህል ማዕከልን በዋና ስራ አስኪያጅነት እንድመራ ጥሪውን ተቀብዬ ተቀላቀልኩ። ቦርዱን እያገዝኩ ብዙ ስራ ሰራን። ቀደም ሲል የባህል ማእከል ግንባታ ቦታ ተጠይቆ ስለነበር አዲስ አበባ ውስጥ 355 ካ/ሜ ይዞታ ከሊዝ ነጻ ተፈቀደልን። ወዲያው ዲዛይኑ ተጠናቆ ግንባታውን አስጀመርን። ከቦርዱና ከማኔጅመንቱ ጋር የእለት ተእለት ክትትል እናደርግ ነበር። ከቴሌቶን በተገኘ ገንዘብ በአገር ቤት ወረዳዎችም በርካታ ፕሮጀክቶች ተገነቡ።

በሂደት “ጉራጌ ልማት ማህበር” እና “የጉራጌ ባህል ማእከል” ተዋህደው “ጉልባማ” የሚባል ድርጅት ፈጠሩ። እኔም በዋና ዳይሬክተርነት ተመደብኩ። 8 አመትም አገለገልኩ። በሂደቱ ዞኑንም ወረዳዎችንም እናግዝ ነበር። አሁን በዮድ አቢሲኒያ ኩባንያ እያገለገልኩ ነው። ለሶስት ዓመታት የኩባንያው ዋና ስራ አስኪያጅ ነበርኩ። በመካከሉ ጡረታዬን አስከበርኩ። አሁን የኩባንያው ልዩ አማካሪ ነኝ። የስራ ፍላጎቴ እየጨመረ አቅሜም እያደገ ነው። ብዙም እሰራለሁ። እቅዴም ብዙ ነው።

### ሴሎች ተሳትፎዎች

በስፖርቱ መስክ የኢትዮጵያ ዳርት ፌደሬሽን ፕሬዝዳንት ሆኜ ለሁለት ዙር (8 ዓመት) አገልግያለሁ። የአገር አቀፉ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ግብረ ኃይል የቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኜም ሰርቻለሁ። ከአገር ውጭ ልኡካንን በመምራት በጣሊያን፣ በቤልጂየም፣ በስዊድን (ሶስት ጊዜ) በፊንላንድ በተለያዩ ስብሰባዎች (መድረኮች) ና ስልጠናዎች ተሳትፌ ተሞክሮዬን አዳብሬያለሁ። (በተለያዩ ወገኖች በዛው እንድቀርና አገሬን እንድከዳ ማባበያ ሁሉ ይቀርብልኝ እንደነበርና ሳልቀበለው መቅረቴን፤ አለመቀበሌንም ተከትሎ ስሜ ተስፋዬ ጎይቴ ሆኖ ሳለ ወያኔው ተስፋዬ ጎይቶም .... በሚል ዘለፋ ሁሉ አጋጥሞኝ እንደ ነበር፣ የታሪክ አካል ነውና፣ በቅንፍ አስቀምጨው ባልፍ የሚከፋ አይመስለኝም።)

### የትዳር ህይወቴ

ባለትዳርና የሁለት ወንዶች (ጀግኖች) ልጆች አባት ነኝ። ከባለቤቴ ጋር ስንጋባ ትምህርቷን 7ኛ ክፍል ላይ አቋርጣ ነበር። በዛው እንድትቀር ሳይሆን፤ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አስቀጥዬ በቢዝነስና አካውንቲንግ ዲፕሎማ፣ በማኔጅመንት ዲግሪዋን እንድትወስድ አድርጌያለሁ። ዛሬ ከኔ በላይ ደመወዝ ታገኛለች። ልጆቼ በትምህርት ሕይወታቸው ሁሉ 1ኛ ሆነው በተሸላሚነት እዚህ የደረሱ ናቸው። ኪንግ ኦፍ ኪንግስ በሚል ነው የሚታወቁት። በ10ኛ ማትሪክ 9 “ኤ” ቀጥታ (ስትሬት “ኤ”)፡ በከፍተኛ ነጥብ ተሸላሚ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትንሹ በከፍተኛ ማዕረግ ነው የተመረቀው። በአሁኑ ሰዓት የራሱን ሶፍት ዌር እያበለጸገ ነው የሚገኘው። የትዳር ጤናማነት በልጆች አስተዳደግም ይገለጻል የሚለውን በራሴ አይቼዋለሁ። እኔ የቤተሰቦቼ ውጤት እንደሆንኩ ሁሉ ልጆቼም (አንተነህ እና ዳኛቸው) የእኔና ባለቤቴ (ትእግስት ዓሊ) ውጤት ሆነው ነው ያገኘኋቸው።

### ማጠቃለያ

እንግዲህ የሁሉም ነገር ሚስጥሩ ስራ ነው፤ መስራት። ለዚህች ገናና አገራችን የላቀ አስተዋጽኦ ካደረጉ ጥቂት ቅን ልጆቿ አንጻር ብዙ ሰራሁ አልልም። 62 አመቴ ነው። ፈጣሪ ከፈቀደልኝ ገና ብዙ እሰራለሁ። ግን ለዚህ ትውልድ እስቲ የዚህን እሩብ ያህል እንኳን ውጤት ቢያሳይ ብዬ ነው ተሞክሮዬን እያጋራሁ ያለሁት። መደበኛ (የማማከሩንም ሆነ ሌላውን) ስራዬን እየሰራሁ፤ በአገራዊ ጉዳዮችና ማህበረሰቡን በሚጠቅሙ ተግባራት እየተሳተፍኩ፤ ያልተጠናቀቁትንም ሆነ አዳዲስ የስነጽሁፍ ስራዎቼን እየሰራሁ ... እቀጥላለሁ። ምንም አይነት የባከነ ጊዜ እንደሌለኝ ሁሉ ወደፊትም የሚባክን ጊዜ የለኝም። ለሌሎችም (በተለይ ለወጣቶች) የምመክረውም ሆነ የምመኘው ይህንኑ፣ ምንም አይነት የሚባክን ጊዜ እንዳይኖራቸው ነው። ዋናው ነገርም ይኸው ነው።

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# መጠናከር ያለበት የቱሪዝም ዘርፉ የሰው ኃይል የማፍራት ተግባር

**መሳኩ ኤርሴ**

እንደ የዓለም የቱሪዝም ድርጅት መረጃ፣ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ትልቅ፣ ውስብስብ እና ለብዙ ሰው የስራ እድል መፍጠር የሚችል ነው። ከቱሪዝም ኢንዱስትሪው ሁለንተናዊ ጥቅም ለማግኘት አገራት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው የሰለጠነ የሰው ኃይል ለመፍጠር ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ይገኛሉ።

አገራችን ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ብዙ ችግር ይስተዋልባታል። የአገራችን የቱሪዝምና ሆቴሉ ዘርፍ ስር የሰደደ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ከሚስተዋልባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ መሆኑን በዘርፉ የተካሄደ ጥናት ያመላክታል።

በሰባተኛው ብሄራዊ የጥናትና ምርምር ጉባኤ ላይ የቀረበው ጥናት እንደሚያሳየው፤ በዘርፉ ከተሰማሩ ሰራተኞች መካከል 33 በመቶው ብቻ ናቸው በዘርፉ ስልጠና ያገኙት። በአገራችን በቱሪዝም ሆነ በሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለሰለጠነ የሰው ኃይል የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ ነው። በስራ ላይ ካሉት ባለሙያዎች መካከል በትክክል ስልጠናውን አግኝተው ምዘናውን አልፈው ስራ የያዙት 14 ነጥብ 4 በመቶ ብቻ ናቸው።

ከዘርፉ ፈጣን እድገት አንፃር የስልጠናው ዘርፍ አብሮ ያለመፍጠን ጥናቱ ከዳሰሳቸው ችግሮች አብዩ ነው። ይህንን እና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ነው። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በአገር አቀፍና በክልሎች ደረጃ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ እየሰሩ ላሉ ባለሙያዎች ስልጠናዎች እየተሰጡ ነው።

በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ በሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ ለሚገኙ ባለሙያዎች በቅርቡ የሶስት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷቸው ተመርቀዋል። ባለሙያዎቹም ከአንድ ሪዞርት እና 34 ሆቴሎች የተወጣጡ ሲሆኑ፣ በአጠቃላይ ከ35 ተቋማት የተወጣጡ 729 ባለሙያዎች ናቸው ስልጠናውን በመከታተል ያጠናቀቁት።

በምረቃው ስርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት የኦሮሚያ ክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሁንዴ ከበደ እንደተናገሩት፤ በኦሮሚያ ክልል ሆቴል ተብለው የሚታወቁ ተቋማት ብዛት 2 ሺ 200 ይደርሳል። ከዚህ ውስጥ የኮከብ ደረጃ ያላቸው ሆቴሎች ብዛት 66 ነው። ከዚህ በተጨማሪም በቅርቡ ለኮከብ ደረጃ የታጩና ለምዘና የተዘጋጁ በርካታ ተቋማትም አሉ። በአጠቃላይ የክልሉ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛት ሆቴል፣ ካፌና ሌሎችን ጨምሮ 18ሺህ 72 ናቸው። በነዚህ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ወደ 82 ሺህ ሰዎች እያገለገሉ ይገኛሉ።

ምክትል የቢሮ ኃላፊው እንዳሉት፤ ስልጠናው በቢሾፍቱ እና በአዳማ የተሰጠ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ወደ 1500 ያህል ባለሙያዎች ተከታትለውታል። በቀጣይነት በባቱ ከተማ፣ በምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተሞች ለአንድ ሺህ ሰልጣኞች ስልጠናው ይሰጣል። በአጠቃላይ 2500 የሚሆኑ ባለሙያዎች ስልጠናውን ያገኛሉ።

የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሰዓዳ ኡስማን በበኩላቸው እንዳብራሩት፤ የኦሮሚያ ክልል ለቱሪዝም ግብዓት የሚሆን ብዙ ያልታወቀ የቱሪስት መስህቦች ያሉበት ቢሆንም፣ መስህቦቹ በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ ሳይውሉ ቆይተዋል። እስከ ለውጡ ድረስ ለቱሪዝም ዘርፍ ተገቢው ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቶ የነበረ ሲሆን፤ ከለውጡ በኋላ ግን ለቱሪዝም ዘርፍም በትኩረት እየተሰራ ነው። ከተሰሩት ስራዎች መካከል የቱሪዝም መዋቅር ከፌዴራል እስከ ቀበሌ መዘርጋቱ ነው። የቱሪዝም ዘርፍን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች እንዲሻሻሉ ተደርጓል።

በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። የኦሮሚያ ክልል መንግስት ለዚህ ዘርፍ ትልቅ ትኩረት በመስጠት የቱሪዝም ተቋማትን የማጠናከር አገልግሎቶችን ተደራሽ የማድረግ እና የማዘመን ስራዎች እየተሰሩ ናቸው። ባለሃብቶች እና ባለሙያዎች ተገቢውን የቱሪዝም አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ድጋፍ እየተደረገ ነው ሲሉ ወይዘሮ ሰዓዳ ያብራራሉ።

አገሪቱ ተጠቃሚ መሆን የምትችለው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ጥሩ አገልግሎት ማቅረብ ሲችሉ ነው ያሉት ወይዘሮ ሰዓዳ፤ ጥራት ያለው አገልግሎት



የኦሮሚያ ክልል በቅርቡ 729 ሠልጣኞችን አስመርቋል

ማቅረብ ካልተቻለ ቱሪስቶችን መሳብ፣ ማቆየትም ሆነ ገቢ ማግኘት አይቻልም። አገሪቱ ተጠቃሚ መሆን እንድትችል የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ሰራተኞች አቅም መገንባት፣ ማሳደግ፣ ማጎልበት ይገባልና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ከተሞች በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ስልጠናዎች እየተሰጠ መሆኑን ገልጸው፣ በአዳማ በሚገኙ አገልግሎት መስጫዎች ውስጥ ለሚያገለግሉ ባለሙያዎች የተሰጠው ስልጠናም የዚሁ አካል ነው ብለዋል። 729 ባለሙያዎች ሰልጥነው በአንድ ጊዜ ሲመረቁ በኦሮሚያ ክልል ደረጃ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ደረጃም የመጀመሪያው መሆኑን ጠቁመዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ባለሙያ ማሰልጠን መቻሉ የቱሪዝም ዘርፉን ለማዘመን እየተደረገ ላለው ጥረት ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

እንደ ወይዘሮ ሰዓዳ ማብራሪያ፤ ስልጠናው በራሱ ግብ አይደለም። ለታሰበው ግብ መዳረሻ ግን ይሆናል። ለክልሉ የቱሪዝም ዘርፍ ተጨማሪ አቅም ለመፍጠር ታስቦ የተሰጠ ነው። ባለሙያዎቹ በስልጠና ያገኙትን እውቀት እና ክህሎት በመጠቀም ለአገልግሎት መሻሻል የበኩላቸውን መወጣት አለባቸው። ባለሙያዎቹም አንዴ ሰልጥነናል ብለው መዘናጋት የለባቸውም፤ በየጊዜው ክህሎታቸውን እያሳደጉ መቀጠል አለባቸው።

ከሌሎች ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጋር በመተባበር መሰል ስልጠናዎችን የመስጠቱ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል። የአሁኑ የመጀመሪያ ስልጠና መሆኑን ጠቅሰው፣ ተጠናክሮ ጠቁመዋል።

በክልሉ ከ15ሺህ በላይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መኖራቸውን የጠቆሙት ወይዘሮ ሰዓዳ፣ በተወሰኑ ከተሞች ለሚገኙ ባለሙያዎች እየተሰጠ ያለው ስልጠና ካሉት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎች ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ብለዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊዋ ገለጻ፤ የቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ረገድ መሰራት ካለበት ስራ አንጻር የሰው ኃይልን በማሰልጠን ረገድ ገና አልተነካም፤ አሁን ያለውን የሰው ኃይል ብቻ ይዞ የቱሪዝም ዘርፉን የታሰበበት ደረጃ ማድረስ አይቻልም። ስለዚህ በዘርፉ ድጋፍ የሚሰጡ አካላት የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ድርሻቸው ትልቅ ስለሆነ በቀጣይ ቢሮቸው ከድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ ነው።

የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በርካታ የቱሪስት መስህቦች መገኛ መሆንዋን ጠቅሰው፤ ከኢትዮጵያ ውስጥም ኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ የቱሪስት መስህቦች ያለበት መሆኑን አስታውቀዋል። እነዚህን የቱሪስት መስህቦች አልምቶ ውጤት ለማምጣት አንዱ መሰረታዊ ነገር የሰው ሀብት ልማት ላይ የሚሰራው ስራ ነው። የቱሪዝም ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ላይ የተሰራው ስራ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው ይላሉ።

በአሁኑ ወቅት በተለይም በኦሮሚያ ክልል የሆቴሎች፣ ሪዞርቶች፣ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች ቁጥር እያደገ መጥቷል። ይህ ይበል የሚያሰኝ እድገት ነው። ለዘርፉ እድገት ባለሃብቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ይህም ይበል የሚያሰኝ ነው። በዘርፉ የሚደረገው ኢንቨስትመንትም ማደጉን መቀጠል አለበት።

ባለሃብቶች ኢንቨስትመንታቸውን ሊያስፋፉ ይገባል ያሉት አቶ ስለሺ፣ በተለይም በተቋሞቻቸው ውስጥ የቀጠሯቸውን ሁሉንም ሰፈራተኞች ማብቃት እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ እንዳለባቸው አስታውቀዋል። አብዛኛው ኢንቨስትመንታቸው ከህንጻ ግንባታ ጎን ለጎን ሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የቱሪዝም ሀብቶች ተጠቃሚ ለመሆን ከዚህ ቀደም በአገር አቀፍ ደረጃ በአሜሪካና በአውሮፓ ላይ ተንጠልጥሎ የነበረውን የቱሪዝም ንግድ በኤዢያ፣ በአፍሪካ እና በመካከለኛው ምስራቅ ጭምር ለማስፋት ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው። በዚህም የቱሪስት ቁጥርን በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ይቻላል። ከነዚህ ቱሪስቶች አገሪቱ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ማግኘት እንድትችል ሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋታል።

አገሪቱ ሰራተኞችን፣ ወጣቶችን በተለይም ሴቶችን ወደ አረብ አገራት ከመላክ ይልቅ እያሰለጠነች በቱሪዝም ዘርፍ የምትጠቀምበት እና በተለያዩ ማህበራት በመደራጀት ለአገር ኢኮኖሚ ልማት የበኩላቸውን እንዲወጡ ማድረግ እንዳለባት ያስገነዝባሉ። በዚሁ መሰረትም ሊሰራ ይገባል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ እቅድ መያዙን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በአስር ዓመት ውስጥ ከቱሪዝም ዘርፉ ከ20 ቢሊየን ዶላር በላይ ለማግኘት መታቀዱን አብራርተዋል። በዚህ ዘርፍ ከሚሊየን በላይ የሚሆኑ ዜጎች በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የስራ እድል ይፈጠርላቸዋል ብለዋል።

የዘርፉ እድገት የዘርፉ ባለሙያዎች በሚሰጡት የአገልግሎት ጥራት የሚወሰን ነው ያሉት አቶ ስለሺ፤ የዘርፉ እጣ ፋንታ የዘርፉ ባለሙያዎች በሚያቀርቡት አገልግሎት፣ በሚኖራቸው ስነምግባርና የተግባቦት ክህሎት እንደሚወሰን ገልጸዋል። እነዚህ የዘርፉ ምሩቃንም የዘርፉን እጣ ፋንታ የመወሰን አቅም ካለው ኃይል መካከል መሆናቸውን አውቀው እንዲሰሩ አሳስበዋል።

በስልጠናው የተሳተፉ ባለሙያዎች በበኩላቸው ስልጠናው ብዙ ልምድና ክህሎት ያገኙበት መሆኑን በመጠቀስ፣ በስልጠናው ያገኙትን እውቀትና ልምድ ወደ ስራ ሲመለሱ እንደሚያግዛቸው ጠቁመዋል። መሰል ስልጠናዎች በተከታታይ ሊሰጡ እንደሚገባም ተናግረዋል።

ስልጠናውን ጨርሰው ከተመረቁት መካከል ዓለምብርሃን በየነ አንዱ ነው። ዓለምብርሃን የምግብ ዝግጅት ባለሙያ ነው። በስልጠናው ብዙ የማያውቃቸውን ነገሮች እንዳወቀበት ነው የተናገረው። በስልጠናው ያገኘው እውቀት ስራውን ለማዘመን ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርለት ተናግሯል። ስልጠናው ሶስት ቀን ብቻ መሆን እንዳልነበረበት ተናግሮ፣ ሰፊ ስልጠና ቢሰጥ መልካም ነው ብሏል።

የፈረቃ ቡድን መሪ መሆኑን የጠቆመው ዓለምብርሃን፣ በስልጠናው ወቅት ያገኘውን ተጨማሪ እውቀትና ክህሎት ከሱ ጋር አብረው ለሚሰሩት እንደሚያጋራም ተናግሯል።

ሜላት ተፈራ የፍሮንት አፊስ ሰራተኛ ነች። በስልጠናው ያገኘቻው ልምድና ክህሎት ስራዋን በተሻለ መንገድ ለመስራት የሚያስችላት መሆኑን ነው የተናገረቺው። ወደ ስራዋ ስትመለስም እንደሚረዳት ተናግራለች። ስራዋን በተሻለ መንገድ ለመስራት እና ፕሮፌሽናል ለማድረግ እንደምትሰራ ተናግራ፤ ስለጠናውን ለባልደረቦቿ እንደምታጋራ ተናግራለች።

ሰዓዳ አማን በአዳማ ሂልሳይድ ሆቴል ሰራተኛ ነው። ስልጠናውን በአጭር ቀን ውስጥ የተሰጠ ቢሆንም፣ ብዙ ልምድና ክህሎት የቀሰመበት፣ በጣም ሲጠብቀው እንደነበር ጠቁሟል። ስልጠናው ለቀጣይ ስራው ብዙ እንደሚያግዘው ጠቁሞ፤ ለስራው የበለጠ እንዲነሳሳ እና ከቀድሞ በተሻለ እንዲሰራ እንዳነሳሳው ተናግሯል። የሚያሰለጥነው አካልም በሆቴል ኢንዱስትሪ ውስጥ ያለውን ክፍተት በመለየት በማሰልጠኑ እንደተደሰተ ተናግሯል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ሰዎች ወደ ስራ የሚገቡት በዘርፉ ሰልጥነው በቂ እውቀት ይዘው ሳይሆን በእድል እና በገጠመኝ ነው። በእድል እና በገጠመኝ ወደ ሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍ የሚገቡ ሰዎች እንዲህ አይነት ስልጠና ማግኘታቸው የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ እንደሚረዳም ጠቁሟል።

**የቱሪዝም ሀብቶች ተጠቃሚ ለመሆን ከዚህ ቀደም በአገር አቀፍ ደረጃ በአሜሪካና በአውሮፓ ላይ ተንጠልጥሎ የነበረውን የቱሪዝም ንግድ በኤዢያ፣ በአፍሪካ እና በመካከለኛው ምስራቅ ጭምር ለማስፋት ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው። በዚህም የቱሪስት ቁጥርን በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ይቻላል። ከነዚህ ቱሪስቶች አገሪቱ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ማግኘት እንድትችል ሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋታል**

# ሳምንቱን በታሪክ

# የ13 ወር ፀጋ እና የቱሪዝም አባት

**ዋለልኝ አየለ**

በተለይም Thirteen Months of Sunshine የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ኢትዮጵያን ለዓለም አስተዋውቋል። የእንግሊዘኛ ፕሮግራሞች ማስጀመሪያ ነበር። ይህን የእንግሊዘኛ ቃል አስገብተው ወደ በይነ መረብ ጎራ ቢሉ ኢትዮጵያን በዓለም ያስተዋወቁ ብዙ አይነት ጥናቶች፣ መጣጥፎች፣ ዜናዎችና መጻሕፍትን ያገኛሉ።

ይህ ቃል ለ50 ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ መሪ ቃል ሆኖ አገልግሏል። አሁን «ምድረ ቀደምት» በሚል ተተክቷል። ዳሩ ግን ኢትዮጵያን ለዓለም አስተዋውቋልና እነሆ ታሪክ ሲዘክረው ይኖራል።

በዛሬው ሳምንቱ በታሪክ ዓምዳችን የዚህ መሪ ቃል ፈጣሪ እና «የቱሪዝም አባት» በመባል የሚታወቁት ሀብተሥላሴ ታፈሰ ናቸውና በእርሳቸው አማካኝነት እናስታውሰዋለን። በዚያ ላይ የዓመቱ የመጨረሻ ወር ላይ ነው የምንገኘው፤ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ ነን። የአጋጣሚ ጉዳይ ሆነና የዚህ መሪ ቃል ፈጣሪና የቱሪዝም አባት ሀብተሥላሴ ታፈሰ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት የዓመቱ መጨረሻ አካባቢ ነሐሴ 3 ቀን 2009 ዓ.ም ነው። እርሳቸውንና በ13 ወር ፀጋ መሪ ቃል የቱሪዝም አባት የሆኑባቸውን ሁነቶች እናስታውሳለን።

በኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ መሥራች፣ የአሥራ ሦስት ወራት ፀጋ (13 Months of Sunshine) በሚል መጠሪያ የአገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት ሲያስተዋውቅ የኖረውን ስያሜ(መለያ) የፈጠሩ፣ እድሜያቸውን በሙሉ ኢትዮጵያን ያስተዋወቁ እንዲሁም በዘርፉ በርካታ ሥራዎችን ያስተዋወቁና የተገበሩ የቱሪዝም አባት ናቸው፤ አቶ ሀብተሥላሴ ታፈሰ።

ሀብተሥላሴ ከአባታቸው ከፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተሚካኤል እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሙላቷ በላይነህ በ1919 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። ሀብተሥላሴ ገና ሕፃን ሳለ አባቱ ፊታውራሪ ታፈሰ የጠረፍ አካባቢ አስተዳዳሪ ሆነው ተመደቡ። በዚህም ምክንያት ፊታውራሪ ሀብተሥላሴ ጎረቤታቸው የሆኑ የውጭ አገር ጥንዶች (ሩስያዊት ሚስት እና ግሪካዊ ባል) ሕፃኑን ሀብተሥላሴን ለጥቂት ጊዜያት ያህል እየተንከባከቡ እንዲጠብቁላቸው በአደራ ሰጥተዋቸው ወደተመደቡበት ሥራቸው ሄዱ። ሀብተሥላሴን በአደራ የተቀበሉት የባሕር ማዶ ሰዎች ሁለት ልጆች ነበሯቸው።

ሀብተሥላሴ ከወላጆቻቸው የተለዩት ገና በሁለት ዓመት ዕድሜያቸው ነበር። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረሯ ሀብተሥላሴን ለመንከባከብ በአደራ የተቀበሉት ባልና ሚስት ሕፃኑን ሀብተሥላሴን ይዘው ወደ ግሪክ ሄዱ። ብዙም ሳይቆይ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተቀስቅሶ ግሪክ በፋሺስት ኢጣሊያና በናዚ ጀርመን መዳፍ ስር ወደቀች። በዚያ የጦርነትና የመከራ ዘመን ባለአደራዎቹ የሀብተሥላሴ አሳዳጊዎች ሀብተሥላሴን ከልጆቻቸው እኩል እየተንከባከቡ ማሳደጉን ቀጠሉበት። ሀብተሥላሴ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ንቁ፣ ታታሪና ብልህ ስለነበር ንቃቱንና ታታሪነቱን ተጠቅሞ አሳዳጊ ቤተሰቦቹን ያግዝ ነበር።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የሀብተሥላሴ አባት ፊታውራሪ ታፈሰ በስደት አውሮፓ ውስጥ ነበሩ። ፊታውራሪ ታፈሰ ልጃቸውን ሀብተሥላሴን በቀይ መስቀል አማካኝነት አፈላልገው ስላገኙት በጦርነቱ መገባደጃ ላይ ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት ተመለሱ።

ብላቴናው ሀብተሥላሴ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተማረው ግሪክ ውስጥ ነው። ዕድሜው 15 ዓመት እስኪሆን ድረስ የሚናገረው የግሪክና የሩስያ ቋንቋዎችን ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በመግባት ለአንድ ዓመት ያህል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማረ።

በመቀጠልም ግብፅ ወደሚገኘው ቪክቶሪያ ኮሌጅ በማቅናት ለሁለት ዓመታት ትምህርቱን ሲከታተል ከቆየ በኋላ እ.አ.አ በ1950 አሜሪካ ሄዶ ከሚኒሶታው ካርልተን ኮሌጅ በስነ መንግሥት እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ተመርቆ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ።

ወጣቱ ሀብተሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ የተመደበው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነበር። እስከዕለተ ሞታቸው ድረስ ካልተለዩት የቱሪዝም ስራ ጋር የተዋወቁት በዚህ ወቅት ነበር። በወቅቱ የሥራ ሚኒስትር የነበሩት ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም ከወጣቱ ሀብተሥላሴ ጋር ለስራ ጉብኝት ወደ አውሮፓ ተጓዙ። በአውሮፓ የቱሪዝም ዘርፍ እንቅስቃሴ የተደነቁት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ በቱሪስቶች ዘንድ ተወዳጅ ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት እንደሆነችና በዘርፉ ጠንክሮ ከተሰራ ብዙ ሀብት ማፍራት እንደሚቻል ለወጣቱ ሀብተሥላሴ ገለፁለት።

ከአውሮፓ እንደተመለሱም ሚኒስትሩ ልዑል ራስ መንገሻ ሀሳባቸውን ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በአጭር ማስታወሻ አቀረቡ። ንጉሠ ነገሥቱም ሃሳቡን ወዲያው ተቀብለው ለስራው የሚመጥን ሰው ሚኒስትሩ እንዲያቀርቡ ነገሯቸው። የሚኒስትሩ ምርጫ ሀብተሥላሴ በመሆኑ ወደ ቤተ መንግስት ተጠርቶ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ እንዲያቋቁም በንጉሰ ነገሥቱ ታዘዘ።

ሀብተሥላሴ ግን በቱሪዝም ዘርፍ የትምህርትም ሆነ የሥራ ልምድና ዝግጅት እንደሌለው ለንጉሰ ነገሥቱ በትህትና አስረዳ። ሥራው ለወጣቱ ሀብተሥላሴ እንደማይሳነው የተገነዘቡት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ « ... ግዴለም ትችላለህ! ስራው ቶሎ ይጀመር!» በማለት አጭር መመሪያ ሰጡት። የንጉሰ ነገሥቱን ትዕዛዝ ተቀብለው ስራ የጀመሩት አቶ ሀብተሥላሴ ታፈሰ ውሎ አድሮ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ታዋቂ ያደረጋቸውን ሙያ የጀመሩት ይህን በመሰለ አጋጣሚ ነበር።

አቶ ሀብተሥላሴ ሥራውን ከግብ እንዲያደርሱ የተጣለባቸው ኃላፊነት ቀላል አልነበረም። በዘርፉ የትምህርትም ሆነ የስራ ልምድና ዝግጅት አለመኖር



አቶ ሀብተሥላሴ ታፈሰ

ከዘርፉ አዲስነትና ከሌሎች ችግሮች ጋር ተደምሮ ስራውን ሲጀምሩት ከባድ አድርጎባቸው ነበር። ስለጉዳዩ በአንድ ወቅት በሰጡት ቃለ ምልልስ « ... በዘርፉ ከመጀመሪያው (እ.ኤ.አ. ከ1954) ጀምሮ አገልግያለሁ። በወቅቱ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣሁ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ እሠራ ነበር። ከዚያም በግድ ይህንን የቱሪዝም ሥራ እንድሠራ አዘዙኝ። ገባሁበት። ከባድ ሥራ ነው። ያን ጊዜ ካሜራ ወደ ኢትዮጵያ አይገባም ነበር። ሲገባም ጉምሩክ ይይዘዋል። ፈቃድ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ማውጣትም ያስፈልግ ነበር። በዚህ ሰበብ ሁለት ጊዜ ታስሬያለሁ። ፎቶግራፍ ለምን ታነሳለህ ብለው ነው ያሰሩኝ። ያን ጊዜ ፎቶግራፍ የሚያነሳ ሰው ሰላይ ተደርጎ ይታሰብ ስለነበር ነው ...» ብለዋል።

ሀብተሥላሴ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ የማቋቋሙን ተግባር ከዳር ለማድረስ ጥረታቸውን ጀመሩ። ቦታ፣ ቅርስ፣ ባሕልና ሌሎች ሀብቶችን አስጎብኝቶ ገንዘብ ማግኘት መቻል በወቅቱ ቀልድ ይመስል ነበርና ስለስራው ስኬታማነት የተጠራጠሩ ብዙዎች ነበሩ።

ይሁን እንጂ የአቶ ሀብተሥላሴ ያላሰለሰ ጥረት ፍሬ እንዲያፈራ አስቻለ። ስራውም ከድርጅቱ እድገት ጋር እየሰፋና እያደገ በመሄዱና ዓለም አቀፍ እውቅና በማግኘቱ አቶ ሀብተሥላሴም የማዕረግ እድገት አገኙ፤ በመጀመሪያ የድርጅቱ ምክትል ሚኒስትር ቀጥሎም ሚኒስትር ዴኤታ ሆኑ። የድርጅቱን የሥራ መመሪያዎች አዘጋጅተው ፈር ከማስያዛቸው በተጨማሪ ኢንዱስትሪው ዘመናዊ አደረጃጀት እንዲኖረው አደረጉ።

ስራው ዕድገት እያሳየ ቢሄድም ብዙ መሰናክሎች መኖራቸውም አልቀረም። የበጀት እጥረትና የግንዛቤ ማነስ ተጠቃሽ ችግሮች ነበሩ። ስለዚህ ጉዳይ ሲያብራሩም « ... ሁልጊዜም እየተጠራሁ ወቀሳ ይቀርብብኝ ነበር። ቤተ ክህነት ተጠርቼ ‹በቴሌቪዥን ለምን እንዲህ ተናገርክ?› እባላለሁ፤ የአገር ውስጥ ገቢ ይጠሩኝና እወቀሳለሁ። በዚያን ጊዜ ከቀረጥ ነፃ ሱቅ ከፍተን ነበር። የእኛ ቢሮ ከመንግሥት ቢሮዎች ሁሉ ሀብታም የሚባለው ነበር። በወቅቱ የቱሪዝም በጀት 220 ሺህ ብር ስለነበር ‹በዚህ በጀት እንዴት አገርን ማሳደግ ይቻላል?› እያልኩ ከጃንሆይ ጋር እጨቃጨቅ ነበር። አንድ ጊዜ ቁልፉን ይዤ ሄድኩና ጃንሆይ ይህንን መሥሪያ ቤት ለሒሳብ ሹም ይስጡት፤ ደመወዝ ከመክፈል ውጪ ሌላ ሥራ መሥራት አልቻልኩም አልኳቸው። የቀረጥ ነፃ ፈቃድ ስጡኝ ብዬ ጃንሆይን ጠየቅሁ። በኋላ የገንዘብ ሚኒስትሩ መጡና ‹እኛ ኮንትሮባንድ መቆጣጠር አቅቶናል፤ ሀብተሥላሴ ደግሞ አናታችን ላይ ኮንትሮባንድ ለመፍጠር ይፈልጋል› አሉኝ። ንጉሡም ‹ሥራህ መቆጣጠር ነው እንጂ ሥራ አይሥራ ነው የምትለው ወይስ መቆጣጠር አልችልም ነው?› ብለው ጠየቋቸውና ተፈቀደልኝ።

ሥራው ሊጀመር ሲል ደግሞ ገንዘብ ስለጠፋ የአባቴን ካርታ ወስጄ አምስት ሺ ዶላር ተበደርኩ። በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ማግኘት ተቻለን። በአንድ ወቅት ከመላው ኢትዮጵያ የእኛ መሥሪያ ቤት ነበር ሀብታም የነበረው። አንድ ሚኒስትር ሲሾም በጊዜው እንዲነግድ አይፈቀድለትም ነበር። ለእኛ ተፈቅዶ ነበርና ብዙ ገንዘብ አስገብተናል። የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ሕንፃ ተሠርቶ ሥራ ሲጀምር የእኛ መኪናዎች ነበሩ የሚያገለግሉት። 46 መኪናዎች ነበሩን። እኔ እንደ ሾፌር፣ እንደ አስጎብኚ፣ እንደ ፎቶግራፍ አንሺ እየሆንኩ ሠርቻለሁ። በኋላ ምቀኛ በዛና ‹የቀረጥ ነፃ ገንዘብ ወደ መንግሥት ይግባ› አሉ። ያ አሠራር በርካታ ሰዎች በዘርፉ መሰማራት እንዲችሉ የሚያደርግ ነው ...» በማለት ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ መለያ ሆኖ ለብዙ ዓመታት ያገለገለውን «የ13 ወር ፀጋ» ስያሜውን እንዴት እንደመረጡት ሲያስረዱ እንዲህ ብለው ነበር።

« ... እኔ ያደግሁት ውጭ አገር ነው። የትም ዓለም ላይ 13 ወር የለም። ፒራሚድ ሲታይ ግብፅ ነው። አይፌል ታወር ሲታይ ፈረንሣይ ነው። የነፃነት ሐውልት ሲታይ አሜሪካ አለ። እኛ የምንታወቅበት የለንም ነበር። ሁሉ ነገር ከዘር፣ ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ ነበር። ሳላውቀው አንድ ወቅት ላይ ‹የ13 ወር ደመወዝ ይሰጠን› ብዬ ጠየቅሁ። ወዲያው ይህንን ሐሳብ ወደ ቱሪስት መሳቢያነት መቀየር እንደሚቻል አሰብኩ። ሌላው ሁሉ ከዘር ከሃይማኖት ጋር የሚያያዝ ነበር። ላሊበላን ባደርግ ኢትዮጵያ በሙሉ ክርስቲያን ባለመሆኑ ችግር ነበረበት። የአሥራ ሦስት ወር ፀሐይ ግን ከምንም ነገር ጋር አይገናኝም። ምንም የፖለቲካና የሃይማኖት ንክኪ የለውም ... »

አቶ ሀብተሥላሴን የተለዩ የሥራ መሪ የሚያደርጋቸው የነበረን ወይም ያለን ተቋም ወይም ድርጅት ተቆጣጥሮ ማንቀሳቀስ ብቻ ሳይሆን ሥራ የመፍጠር ችሎታቸው ነው። የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብት ለውጭና ለአገር ቤት ተመልካቾች ማሳወቅ (ፕሮሞሽን)ን መሰረታዊ ዓላማው አድርጎ ሲንቀሳቀስ የነበረው የቱሪዝም ድርጅት ሥራውን ለማከናወን አቅም ባነሰው ወቅት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚያስችለውን የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅትን አቋቋሙ። ዛሬ ይህ ድርጅት የአገሪቱን ቅርስና ባህል ከማስተዋወቁ በተጨማሪ ብዙ ትርፍ የሚያስገኝ ተቋም ሆኗል። በመቀጠልም ከፕሮሞሽኑ ሥራ ጋር ተደጋጋፊ የሆነውን የአገር ባህል ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅትን አቋቋሙ። የመኪና ኪራይ ድርጅት እንዲመሰረት ያደረጉትም እርሳቸው ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች ገቢ ከማስገኘታቸው ባሻገር ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠሩ ናቸው።

በስራቸው ምክንያት ያልደረሱበት የኢትዮጵያ አካባቢ እንደሌለ የተናገሩት አቶ ሀብተሥላሴ፣ « ... በእግር፣ በፈረስ፣ በግመል፣ በሄሊኮፕተር፣ በአውሮፕላን ሁሉ ተዘዋውሬ ከ100 በላይ ሰው ያልረገጣቸው የኤርትራ ደሴቶችን አይቻለሁ። ትልቅ ሀብት ናቸው። ቢያውቁበት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መሰብሰብ ይችሉ ነበር። በጋምቤላ በኩል ጂካው ድረስ ሄጃለሁ። የደቡብ ሱዳን ጠረፍ ነው። በኤርትራ በኩል ቤንአመር ድረስ ወዳለው የጠረፍ ቦታ ደርሻለሁ። ቤንሻንጉልን በሙሉ እስከ ሱዳን ድረስ አዳርሻለሁ። መሥራት ካስፈለገ ማየትና ማወቅ ግድ ይሆናል። ካየንና ካወቅን በኋላ ማውራት ይቻላል ... » በማለት ተሞክሯቸውን አካፍለዋል።

የሒልተን ሆቴልን ጨምሮ የኢትዮጵያ ምግብ ዝግጅት ኢንስቲትዩት እንዲሁም ለፕሮሞሽን ሥራ የዋሉ አያሌ ዲዛይኖች እና መፅሔቶች አቶ ሀብተሥላሴ በቀጥታ ተሳትፈውባቸው ሥራ ላይ ከዋሉ በርካታ ፕሮጀክቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት «የ13 ወር ፀጋ» የሚለው የኢትዮጵያ የቱሪዝም መጠሪያ «ምድረ ቀደምት (Land of Origins)» በሚል ስያሜ ተተክቷል። « ... ‹የ13 ወር ፀጋ› የሚለው የኢትዮጵያ የቱሪዝም መለያ ለብዙ ጊዜያት ያገለገለ ነው። አሁን መቀየር አለበት› የሚሉ ሰዎች አሉ። ይቀየር ቢባል ምን ይሰማዎታል?» ተብለው ተጠይቀው አቶ ሀብተሥላሴ « ... ሁልጊዜ አንድ ነገር ሲፈጠርና የሚበልጠው ሲገኝ ያንን ማየቱ ተገቢ ነው። አሁን ከዚያ የበለጠ ከተገኘ ደግሞ ቶሎ መተካት ነው። ምንም ችግር የለውም» ብለዋል።

አቶ ሀብተሥላሴ በርካታ ሽልማቶችንም አግኝተዋል። በ2009 ዓ.ም የዋንጫና የወርቅ የደረት አርማ (Pin) ሽልማት በወቅቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ተበርክቶላቸዋል። የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በበኩሉ የገንዘብ ሽልማትና እውቅና ሰጥቷቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም በቅርስና ባሕል ዘርፍ የ2007 ዓ.ም «የበጎ ሰው ሽልማት» ተሸላሚ ሆነዋል።

እኚህ የቱሪዝም አባት ባደረባቸው ሕመም በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሕክምና ክትትል ሲያደርጉ ቆይተው ነሐሴ ሦስት ቀን 2009 ዓ.ም በተወለዱ በ90 አመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ስርዓተ ቀብራቸው ነሐሴ ሰባት ቀን 2009 ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈፅሟል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## በጊዜ የጠለቀው ጀምበር - ኢዮብ መኮንን

**አቤል ገ/ኪዳን**

በወጣቶች ተወዳጅ ከሆኑ ድምጻውያን አንዱ ነበር። ሙዚቃዎቹ ከመዝናኛት ባለፈ ጠቃሚ ጭብጥ ያላቸው ናቸው በሚል በሀያሲያን ዘንድ ይደነቃል። ነገር ግን ይህ ባለ ታላቅ ተሰጥኦ አርቲስት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ገና በዘመኑ እኩሌታ ላይ ነበር። ይህ በጊዜ የተቀጠፈ አበባ ስሙ ኢዮብ መኮንን ይባላል። ከዚህ ዓለም በሞት የተለየንም በዚህ በያዝነው ወር ነሐሴ 12 ቀን 2005 ዓ.ም ነው። ዛሬ የዚህን ተወዳጅ ድምጻዊ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ እንዳስሳለን።

ድምጻዊ እዮብ መኮንን ዘውዴ ከአባቱ ከአቶ መኮንን ዘውዴ ይመኑ እና ከእናቱ ወይዘሮ አማረች ተፈራ የምሩ ጥቅምት 12 ቀን 1967 ዓ.ም በጅጅጋ ከተማ ጭናቅሰን ገብርኤል አካባቢ ተወለደ። እድሜው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በጅጅጋ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ ከፊል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ ከወላጅ አባቱ ጋር ወደ አስመራ በመሄድ የተከታተለ ሲሆን፤ ቀሪውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ ወደ ጅጅጋ በመመለስ ተምሯል። በ1991 ዓ.ም. በአጋጣሚ ወደ አዲስ አበባ የሚያመጡ ፈቃደኛ ሰዎች በማግኘቱ እራሱን ያስተዳድርበት የነበረውን የፎቶግራፍ አንሺነት ሥራን ትቶ፣ በ24 ዓመቱ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ካዛንቺስ አካባቢ በሚገኘው የያኔው ፋልከን ክለብ ድምጻዊነቱን “ሀ” ብሎ ጀመረ።

በኢዮብ የሙዚቃ ሕይወት ውስጥ የሬጌ ንጉሱ ቦብ ማርሌይ እና የኦሮምኛ ሙዚቃ ንጉሱ አሊ ቢራ ተጽእኖ ከፍ ያለ ነው። በተለይ አሊ ቢራ ለእዮብ ወደ ሙዚቃ መግባት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። “ልጅ እያለሁ ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ ብዙውን ጊዜ የመስማት እድል አጋጥሞኝ የነበረው የአሊ ቢራን ሙዚቃ ነበር” ብሏል በአንድ ቃለ መጠይቁ ላይ። በዚህ መልኩ የተጀመረው የኢዮብ የሙዚቃ

ሕይወት አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ በክለቦች በመጫወት እያደገ ሄዷል። በተለይም ዛየን ባንድ ውስጥ የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነበር።

ከዚያም እዮብ የመጀመሪያ አልበሙን አወጣ። ወቅቱም በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ሰሞን ነበር። አልበሙ እንደቃል የሚል ስያሜ ያለው ሲሆን ነገር ግን አዘፋፈኑ ከተለመደው የኢትዮጵያ ሙዚቃ አካሄድ ለየት ያለ በመሆኑ መጀመሪያ ላይ ለመደመጥ ጊዜ ወስዶበት ነበር። “ለሰባት ወራት ገደማ አልተደመጥኩም ነበር” ይላል። እንዲያውም የሙዚቃው አለመደመጥ ወደ ሌላ ሙያ እንዲያተኩር ገፋፊቶት እንደነበር ይናገራል። ከዚያ ግን ጸጥታው እየተገፈፈ የኢዮብ ሙዚቃዎችም የህዝብን ጆሮ መያዝ ጀመሩ። ከዚያ በኋላ ያለው ታሪክ ነው። ኢዮብ ብዙዎች ጆሮ ላይ ታትሞ ቀረ። እስከዛሬም አልወጣም።

ኢዮብ ሙዚቃን ለማህበረሰብ ግንባታ ማስተማሪያነት መጠቀም አላማ አድርጎ የሚሰራ ሰው ነው። “በኔ ሙዚቃ ሰዎች እንዲስቱ አልፈልግም” ይላል። ይህ አላማው በሙዚቃውም ሆነ በሙዚቃ ማጀቢያ ቪዲዮም ውስጥ ይታያል። የሚያውቁትም ሰዎች እዮብ በስራዎቹም ሆነ በአኗኗሩ ቁጥብ እንደሆነ ይናገራሉ። የመጀመሪያ አልበሙ ተወዳጅ በሆኑ ሙዚቃዎች የተሞሉ ናቸው። በተለይም እንደ ነቅቻለሁ ፤ ነገን ላየው ፤ ደብዝዘሽ ፤ ይዘባርቃሉ፤ ያሉት ሙዚቃዎች ዛሬም ድረስ እንደ አዲስ የሚደመጡ ሆነው አሉ።

የኢዮብ ሁለተኛ አልበም ከመጀመሪያው አልበም ከ10 ዓመት በኋላ ነበር የወጣው። ይህኛውም አልበም እንደመጀመሪያው በአድማጩ ዘንድ እጅጉን ተወዶለታል። የአልበሙ መጠሪያ እሮጣለሁ የሚል ሲሆን ጠንካራ የሆኑ መልእክቶችን ያዘሉ ተወዳጅ ሙዚቃዎች ስብስብ ነው። ይህ አልበም ለየት የሚያደርገው እዮብ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ የወጣ መሆኑ ነው። በሕይወት ሳለ ሁለተኛ አልበሙን መሥራት እንደጀመረ ስለተገለጸ፣ ብዙዎች የአልበሙን መለቀቅ በጉጉት ይጠብቁ ነበር። ካለፈ በኋላም ሙዚቃዎቹ እንደሚለቀቁ ከተገለጸ ቆየት ብሏል። ታኅሣሥ 25 ቀን 2009 ዓ.ም. ገበያ ላይ የዋለው አልበሙ በቅንብር ዳግማዊ አሊ፣ ሚካኤል ኃይሉና ካሙዙ ካሳ በግጥምና ዜማ ምዕራፍ አሰፋ፣ ኃይሉ አመርጋ፣ ዓለማየሁ ደመቀ፣ ሙሉቀን ዳዊት፣ ኤርሚያስ ታደሰና ሌሎችም ባለሙያዎች ተሳትፈውበታል። ማስተሪንጉ በአበጋዝ ክብረወርቅ ሺኦታ ተሠርቷል። አልበሙ ፕሮዲውስ የተደረገው በይሳቃል ኢንተርቴመንት ሲሆን፣ በቮካል ሪከርድስ ተከፋፍሏል።

እዮብ ተወዳጅ ስራዎችን በማቅረቡ የተነሳ በሕይወት እያለ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ከውጭ ፈላጊዎች በዝተውበት የነበረ ሲሆን በየቦታው የሙዚቃ ዝግጅቶች ነበሩት። አድናቂዎቹ በበኩላቸው የእሱን አዳዲስ ስራ ለመስማት እየጠበቁም ነበር። ነገር ግን ያ ባለብዙ ተስፋ ጥበበኛ ሳይታሰብ አደጋ ገጠመው። የነበረውን ሁኔታ አንድ ሰው በሚከተለው መልኩ አስፍሮታል

“ነሐሴ 5 እንደ ሁልጊዜውም እዮቤ ቅዳሜ ምሽቱን ተረኛ በሆነበት የቬላ ቬርዴ ክለብ ሲሰራ አምሽቶ እጅግ በተዳከመ ገፅታ ወደቤቱ ገባ፣ ባለቤቱ ጋደም ብላ እየጠበቀችው ነበር እዮቤ እንደወትሮው እቤት እንደገባ ሶፋ ላይ አረፍ ማለትን አልመረጠም ነበር እንደደከመው ለባለቤቱ ነግሯት ወደመኝታ ቤት አመራ ማግስቱን በጠዋት ተነሳና ወደ ሀኪም ቤት አመራ፣ በዛም ጤነኛ እንደሆነና እረፍት ብቻ እንዲያደርግ ተመክሮ ተመለሰ።

ነሐሴ 7 እዮቤ ዛሬም በጠዋት ነበር የተነሳው። ምክንያቱ ደግሞ የልጁ የትምህርት ቤት ምዝገባ ቀን ስለነበረ ነው። ልጁ ኬቨን ወደ ትምህርት ቤት ስለሄደ እዮቤ ቁርሱን በላላና አንላየን ጊታር ይማር ስለነበር ለፕቶፑን ከፍቶ ጊታሩን ጨብጦ ለመማር ዝግጁ ቢሆንም ኔትወርኩ ጥሩ አልነበረም። ደጋግሞ ቢሞክርም አልሆነም። ይሄኔ ኔትወርኩ ጥሩ እስከሚሆን ለምን የኬቨንን የትምህርት ቤት ክፍያ ከፍዬ አልመጣም የሚል ሀሳብ አሰበ። ወዲያው ተነሳና ለባብሶ የሚወዳትን ሳይክሉን እያሽከረከረ 4:30 ላይ ከቤት ወጣ፣ ክፍያውን ከፍሎ ተመለሰና በሩ ላይ ሲደርስ እዮብ ግማሽ አካሉ ከበደው አልታዘዝለት አለው። በቆመበት በተደገፈው በር ስር ሽርተት ብሎ ወደቀ። አካባቢው ላይ የነበሩ እዮብ ያቀርባቸው የነበሩ ወጣቶች ተሯሩጠው መጥተው አፋፍሰው ወደቤት ይዘውት ገቡ። ታክሲ ተጠራና ጉዞ ወደ አያት ሆስፒታል። እዛ ደርሰው መጠነኛ ምርመራ ከተደረገለት በኋላ ለተሻለ ህክምና ወደ ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል አመሩ። በመንገዳቸው እዮብ ስልኩን አወጣና ለጓደኛው ኦሪዮን እንድትደውል ስልኩን ለባለቤቱ ሰጣት። ኦሪዮንና እነእዮብ እኩል ቅዱስ ገብርኤል ደረሱ። ሀኪም ካየው በኋላ ወደ ሲቲ ስካን ክፍል መግባት አለበት ተባለ። እዮቤ ደቂቃዎች በሄዱ ቁጥር እየተዳከመ መጥቷል። ወደ ሲቲ ስካን ክፍል ከኦሪዮን ጋር እየሄደ የሕይወቱን መጨረሻ በጤነኛ ቃላት እንዲህ አለው....... "ለፈጣሪ ፀልዩልኝ"

እዮብ ልክ ከሲቲስካን እንደወጣ ነገሮች በፍጥነት መቀያየር ጀመሩ። እዮብ ያወራል ግን የሚናገረው ነገር ጥርት ብሎ አይሰማም። ቅዠት ነገርም ይመስላል። በፍጥነት ወደ IC ክፍል እንዲገባና እንዲተኛ ተደረገ፣ ቤተሰቦቹ ከውጭ ሆነው ሁኔታውን ሲጠባበቁ መሸ። አመሻሽ ላይ በብዙ ልመና ገብተው እንዲያዩት ተፈቀደላቸውና ገብተው ሲያዩት አይኑን ገርበብ አድርጎ በዛ በሚያምር ግርማ ሞገሱ ጋለል ብሎ ተኝቷል። ሊያዋሩት ሞከሩ መልስ አይሰጥም፣ ሀኪሙ እንደምታዩት እዮብ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ነው ያለው መልስ አይሰጥም፣ ህክምናውን ለማድረግ የግድ እስኪነቃ መጠበቅ አለብን አለ። መንገደኛው እዮቤ ግን ላለመንቃት ወደ ማንቀላፋት ነበር !

እዮብ መኮንን ነሐሴ 5 የገጠመው አደጋ ነሐሴ 12 ቀን 2005 ዓ.ም ነፍሱ ከስጋው እንድትለይ አደረገ።

እዮብ ባለጠንካራ ስብእና ሰው ነው።



ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ የደራሲ በእውቀቱ ስዩምን ምስክርነት እንስማ። “ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ የበጎ አድራጎት ትርኢት ላይ ለመሳተፍ፣ ከዘፋኞች ጋር ወደ ደሴ ተጉዤ ነበር። የተሣፈርንበት አውቶብስ ጉንጫቸውን በጫት አሎሎ በወጠሩ ዘፋኞች ተሞልቷል። ዘፋኞቹ ሲሻቸው ይተራረባሉ፣ ሲሻቸው ይጮሃሉ፣ ይጨፍራሉ። የአውቶብሳችን ሽማግሌ ሹፌር ሳይቀር፣ አልፎ አልፎ መሪውን እየለቀቀ በማጨብጨብ፣ በ ‹‹ቅወጣ›› ከዘፋኞች እንዳማያንስ በማሳየት ላይ ነበር። በጫቱም፣ በጭፈራውም የሌለበት ድምጻዊ እዮብ መኮንን ብቻ እንደሆነ ተመለከትሁ። በእርጋታ ተቀምጦ፣ በአውቶብሱ መስኮት አሻግሮ የሚሮጡ የግራር ዛፎችን ይመለከታል።›› ልዩነቱ ግልጽ ነበር።

ድሮ ድሮ፣ እዮብ መኮንን አቤሴሎም የሚዘናፈል ረጅም ጸጉር ያለው ጎልማሳ ነበር። ድንገት ጸጉሩን ተሸለተ፣ ከጸጉሩ ጋር የጥንት ባህርይውን አራገፈ። ጭምት፣ መንፈሳዊና በመጽሐፍ ቅዱስ ፍቅር የነደደም ምዕመን ሆነ።

በተገናኘን ቁጥር፣ እዮብ ስለእምነት እንድንወያይ ይፈልጋል። ብዙ ጊዜ እምነት የሚያጠብቅ ሰው አንዳች ችግር ይኖርበታል ብዬ አስብ ነበር። እዮብ ግን እጅግ መልካም ሊባል በሚችል ሕይወቱ፣ ይሄንን አመለካከቴን ውድቅ አድርጎብኛል።

የዛሬ ሳምንት ገደማ ኢዮብ ዘፈን በመሥራት ላይ ነበር። እና ለአንድ ዜማው ግጥም እንድሠራለት ጋበዘኝ። ከዚህ በፊት የሞከርኳቸው የዘፈን ግጥሞች ስለከሸፉብኝ ግብዣውን ለመቀበል አመነታሁ። ግን ደሞ ወዲያው፣በኢዮብ ድምጽ ግጥሜ ተዘፍኖልኝ ለማየት ጓጓሁ። ውሀ ልማት አካባቢ፣ ሌክስ ፕላዛ ሕንጻ ሥር መኪናው ውስጥ ቁጭ ብለን ዜማዎችን ማድመጥ ጀመርን። ዘፈኑ ውስጥ ያሉት ሐሳቦች አብዛኞቹ ወደ መዝሙር ያዘነብላሉ። እዮብ ዘፈኑን ለፈንጠዝያ ሳይሆን ለስነምግባር ግንባታ ሊጠቀምበት ፈልጓል። አንድ በጣም ልብ የሚበላ የሶማሌ ዘፈን አስደመጠኝ።

‹‹ሶማሊኛ ትችላለህ እንዴ?››

‹‹አዎ፣ትግርኛም አውቃለሁ!››

‹‹የት ተማርከው?››

‹‹አስመራ፣ የወታደር ልጅ መሆኔን አትርሳ››

ከዘፈን ውጭ ምን ታደርጋለህ?

‹‹ኦን ላይን፣ ጊታር እየተማርሁ ነው። ቆይ ላሳይህ››...ላፕቶፑን ለኮሰና ጥቂት አስጎበኘኝ። ከዛ ከመኪናው ስወርድ የመኪናው እጀታ ስለማይሠራ ወርዶ ከውጭ ከፈተልኝ። እዮብ ብዙ ብሮችን መቁጠር የሚችል ልጅ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ይሁን እንጂ እንኳን መኪናውን የመኪናውን እጀታ ማስቀየር አልፈለገም። ምናልባት፣ ዓመት በአልን ጠብቆ ልብስ የሚቀይር ብዙ ሰው ባለበት አገር ውስጥ፣ መኪና መቀያየሩን እንደ ኃጢአት ቆጥሮት ይሆናል።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ልኡል የተባለ ዘፋኝ ጓደኛዬ፣ የእዮብን በድንገት መውደቅ ሲነግረኝ ወደ ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ሄድኩ። ዘፋኞችና አዘጋጆች መጠበቂያው ክፍል ላይ ተደርድረው ይተክዛሉ። ዘሪቱ፣ ዳግማዊ አሊ፣ እቁባይ በርሄ፣ እጃቸውን አገጫቸው ላይ ጭነው፣ ተቀምጠዋል። የእዮብ ባለቤት ወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጠች ታነባለች።

ዛሬ ደግሞ ይሄው ሞቱን ሰማሁ። ኢዮብ!!! በጠፈሩ ውስጥ፣ ያለግብ ከሚዞሩ ኮረቶች፣ ያለ ምክንያት ከሚበሩ ኮከቦች በቀር ምንም የለም ብዬ እንደማምን ታውቃለህ። ይሁን እንጂ ለዛሬ እንኳ፣ የኔ እምነት ከሽፎ ያንተ እምነት እውነት እንዲሆን እመኛለሁ። በምድር ለገጠመህ መራራ እጣ ሰማያዊ ካሳ (ጉማ) እንድታገኝ እመኛለሁ።

ከጊዜው ቀድሞ ስለተለየን ተወዳጅ ድምጻዊ ሳሙኤል ወልደየስ የተባለ ሰው በ2011 ዓ.ም የሬጌው ንጉስ በኢትዮጵያ የሚል መጽሀፍ የጻፈለት ሲሆን በቀጣይ ሳምንት እሁድ እዮብን የሚዘክር መርሀ ግብር በሀገር ፍቅር ቴአትር መዘጋጀቱም ተሰምቷል።

# ዓለም አቀፍ




አንቶኒ ብሊንከን

## የብሊንከን የአፍሪካ ጉብኝት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን በነሃሴ ወር መግቢያ ቀናት በሦስት የአፍሪካ ሀገራት ጉብኝት አድርገዋል።

የጉበኝታቸውን ማጠቃለያ ከትናንት በስቲያ በርዋንዳ አድርገው ነበር። በወቅቱም የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ከርዋንዳው ፕሬዚዳንት ፖል ካጋሜ ጋር ኪጋሊ ላይ ተወያይተዋል።

ብሊንከን በወቅቱ "አሜሪካ የአፍሪካ እውነተኛ አጋር መሆን እንደምትፈልግ፣ ግጭቶችን ለማስወገድ የሚደረገውን ጥረት እንደምትደግፍ እንዲሁም ሀገሮች ከማን ጋር መወዳጀት እንዳለባቸው ትዕዛዝ ሰጪ መሆን እንደማትፈልግ" አፅንዖት ሰጥተው ተናግረዋል።

የሰብዓዊ መብቶች አያያዝና በጣም ያሳሰቧቸውን ጉዳዮች በውይይቱ ወቅት ማንሳታቸውን ብሊንከን ለሪፖርተሮች አመልክተው ርዋንዳ ኮንጎ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ውስጥ ያሉ አማፂያንን መደገፍ እንድታቆም አሳስበዋል።

"ሁሉም ወገኖች የታጠቁ ቡድኖችን እንደሚደግፉ፤ ኮንጎም "የዴሞክራሲ ኃይሎች ለርዋንዳ አርነት" የሚባለውን ቡድን እንደምትደግፍ፤ ሩዋንዳም የኮንጎውን አማፂ ኤም-23ን እንደምትደግፍ ተዓማኒ ሪፖርቶች አሉ። የኛ አቋም ግልፅ ነው፤ በማንም ይሁን በማን ለየትኛውም ታጣቂ ቡድን የሚሰጠው ድጋፍ መቆም አለበት" ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

"ርዋንዳ ምሥራቅ ኮንጎ ያሉ ኤም-23 የሚባሉትን ታጣቂ አማፂያን ትደግፋለች" መባሉ እንደሚያሳስባቸው ብሊንከን ከቀናት በፊት በኮንጎ ዋና ከተማ ኪንሻሳ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት አጽንኦት ሰጥተው ተናግረው ነበር።

የኮንጎው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ክርስቶፍ ሉቱንዱላ ደግሞ "በሃገራችን በስተምሥራቅ ያለው አካባቢ ላለፉት ሃያ ዓመታት በአሸባሪዎች መከራውን አይቷል፤ ሕዝባችን ተፈጅቷል፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ነው በሁለትዮሽ ጉዳይ ላይ ሃሳብ የተለዋወጥነው" ብለዋል።

ብሊንከን የአፍሪካ ጉብኝታቸውን ባለፈው ሰኞ በደቡብ አፍሪካ የጀመሩት ተማሪዎች ከአፓርታይድ አገዛዝ ጋር ያደረጉትን ትግል የሚያሳየውን "የሶዌቶ አመፅ" ቤተመዘክር በመጎብኘትና ለተማሪዎቹም ክብር በመስጠት ነበር።

ብሊንከንና የደቡብ አፍሪካው አቻቸው ናሌዲ ፓንዶር የጋራ ግብና ፍላጎታቸውን በተመለከተ ፍሬያማ ውይይት ማድረጋቸውን ሁለቱም ወገኖች ተናግረዋል።

## ሜድቬዴቭ ሩሲያ በዩክሬን የኒውክሌር ጣቢያው ላይ ጥቃት አድርሳለች ክስ አጣጥለዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የሩሲያ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ዲሚትሪ ሜድቬዴቭ፤ በዩክሬን የኒውክሌር ጣቢያው ላይ ጥቃት አድርሳለች ክስ አጣጥለዋል።

ክሱን ውድቅ ሲያደርጉም "የኒውክሌር አደጋዎች በአውሮፓም ሊከሰቱ ይችላሉ" ሲሉ ተናግረዋል። ሜድቬዴቭ ይህን ያሉት በዩክሬን ዛፖሪዝሂያ የኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ዙሪያ ኃይሎችን በማስፈር የኒውክሌር አደጋን በመፍጠር ሩሲያን ለሚወነጅሉት የዩክሬን አጋሮች ባስተላለፉት መልዕክት ነው።

ተመድ በዩክሬን የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ አካባቢ ከጦር ነጻ ቀጠና እንዲቋቋም ጠይቋል። ሩሲያ እና ዩክሬን ከአውሮፓ ትልቅ የሆነውን እና በዩክሬን የሚገኘውን የዛፖሪዝሂያ ኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ላይ ጥቃት በማድረስ እርስ በእርሳቸው በመካሰስ ላይ መሆናቸው ይታወቃል።

ሜድቬዴቭ ግን "እነሱ (ኪቭ እና አጋሮቿ) ሩሲያ ናት ይላሉ። ይህ በግልጽ 100 በመቶ ከንቱ ነው" ሲሉ በቴሌግራም ቻናላቸው ባጋሩት ጽሁፍ ተናግረዋል። እንደ ሮይተርስ ዘገባ "የአውሮፓ ሕብረት የኒውክሌር ኃይል ማመንጫዎች እንዳሉትም መዘንጋት የለብንም፤ እናም እነዚያ አደጋዎች ሊከሰቱ ይችላሉ" የሚል ማስጠንቀቅያ አዘል መልእክትም አስተላልፈዋል ሜድቬዴቭ።

በደቡብ ምስራቅ ዩክሬን የሚገኘው ዛፖሪዝያ አቶሚክ ሃይል ማመንጫ በአውሮፓ ትልቁና በዓለም ላይ ካሉት 10 ትላልቅ የኒውክሌር ኃይል ጣቢያዎች መካከል አንዱ ነው።

እናም በጦርነት ውስጥ የሚገኙትና እርስ በርስ የሚካሰሱት ሩሲያና ዩክሬን በጣቢያው ላይ የሚያደርሱት ጥቃት ከሀገራቱ በዘለለ ለተቀረው ዓለም ያልተፈለገ መዘዝ ይዞ እንዳይመጣ ተሰግቷል። ሁኔታው ያሰጋው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) በዩክሬን የኃይል ማመንጫ ጣቢያ አካባቢ የደረሰው ጥቃት በአካባቢ ከጦር ነጻ ቀጣና ይኑር የሚል ጥሪ ለማድረግ ተገዷል።

ተመድ ይህን ያለው በሩሲያ ጦር ቁጥጥር ስር የዋለው የዛፖሪዝሂያ የኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ጥቃት ደርሶበታል መባሉን ተከትሎ ነው። ሩሲያ የዩከሬን ጦር በገዙፍ" ዛፖሪዝያ ኒውክሌር ጣቢያ" ላይ ተኩስ ከፍቷል ስትል ከሰሰች። ሁኔታውን ለመገምገም ሃሙስ እለት የተሰበሰው ተመድ፣ ሁለቱም አካላት የኃይል ጣቢያው አካባቢ ውጊያ እንዲያቆሙ ጠይቋል።

"ተቋሙ የወታደራዊ ዘመቻ አካል መሆን የለበትም፤ ይልቁንም የአካባቢውን ደህንነት ለማረጋገጥ ከወታደራዊ እንቅስቃሴ ነጻ ማድረግ ዙሪያ አስቸኳይ የቴክኒካል ደረጃ ስምምነት ያስፈልጋል" ሲልም ነው ተመድ ዋና ጸሃፊው ጉቴሬዝ ያሳሰቡት።

በስብሰባው ያላትን ስጋት የገለጸችው አሜሪካም፤ ቦታው ከወታደራዊ እንቅስቃሴ ነጻ እንዲሆንና ዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ (IAEA) ቦታውን እንዲጎበኝ አሳስባለች።

**ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም**

## የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በምድር አውሮፕላን

**ታምራት ተስፋዬ**

መንግስት የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኛውን የልማት እና የእድገት ተጠቃሚ ለማድረግ እየወሰዳቸው ካሉት እርምጃዎች ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ከቤት ወደ ሰራ እና ከሰራ ወደ ቤት የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አንዱ ሲሆን ይህንንም አገልግሎት ድርጅትን የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 298/2006 ተቋቁሟል።


የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት የፐብሊክ ሰራተኛው በከተማው ባለው የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ምክንያት ይደርስበት የነበረ ወከባ ፣ እንግልትና ወጪ በማስቀረት ምቾቱና ድህንነቱ ተጠብቆ በሚፈለገው ጊዜና ፍጥነት በአስተማማኝ ሁኔታ ወደ ስራና ቤቱ በማድረስ ረገድ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት መስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በየጊዜው አደረጃጀቱንና የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል ላይ ይገኛል።

የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ከመስጠት ባሻገርም ከስራ መግቢያና መውጪያ ሰዓት ውጭ የዘመኑ የቴክኖሎጂ በተገጠመላቸው ምቾታቸው አስተማማኝ በሆኑ አውቶቡሶቻችን ህዝብ ትራንስፖርት ታክሲ አገልግሎት እየሰጠም ይገኛል።

አሁን ላይ ደግሞ የአገልግሎት አድማሱን ከፍ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደተለያዩ ክፍለ አገሮች የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ መስጠት ተሸጋግሯል። ይህን አገልግሎትን ለማሳለጥ የሚያግዙ ዘመናዊ አውቶቡሶችንም አስገብቷል።‹‹የምድር አውሮፕላን››የተባሉት ዘመናዊ አውቶቡሶችም ከቀናት በፊት በድርጅቱ ቅጥር ግቢ በሰራተኞች ተጎብኝተዋል።

በዚሁ የጉብኝት መርሀ ግብር ላይም የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬህይወት ትልቁ እንደሚገልጹትም፤ ድርጅቱ ከፍተኛ እድገት እያስመዘገበ የአገልግሎት አድማሱንም እያሰፋ ይገኛል። አሁን ላይ ደግሞ የአገልግሎት አድማሱን ከፍ





በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደተለያዩ ክፍለ አገሮች የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ መስጠት ተሸጋግሯል።

ይህን ግልጋሎት ለመስጠትም ዘመናዊ አገር አቋራጭ አውቶቡሶች ግዢን ፈፅሟል። አውቶቡሶቹም በተለይ የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋን ለመከላከል የሚያስችሉና ለተሳፋሪው ምቹና ፈጣን እና ዘመናዊ ናቸው። ከፍተኛ የፈረስ ጉልበት ያላቸው፣ የ45 ሰዎች መቀመጫ፣ በቂ የሆነ የእቃ መጫኛ፣ በውስጡም የመጸዳጃ እና የማቀዝቀዣ ክፍል ያላቸው እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉም ናቸው።

ሙሉ በሙሉ አርቴፊሻል ኢንተለጀንት ሲስተም የተገጠመላቸው ሲሆን ሌላው ቀርቶ አሽከርካሪው መጠጥ ጠጥቶ ከገባ ‹‹አሽከርካሪው መጠጥ ጠጥቷል›› ብሎ መልእክት ማስተላለፍ ይችላሉ። በማሽከርከር ላይ ሳለ እንቅልፍ ካስቸገረውም ሆነ ስልክ እያወራ ከሆነም ተመሳሳይ የእርማት መልእክትን ያስተላልፋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተራ ገለፃ፤ ተጠቃሚዎች ትኬት ለመቁረጥ ወደ ድርጅቱ መምጣት አይጠበቅባቸውም። ካሉበት ሆነው ወደ ፈለጉት አቅጣጫ በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ትኬት መቁረጥ የሚችሉበት አሰራር ተዘጋጅቷል። በዚህ ሂደት የአውቶቡሶቹን የጎን ቁጥር እንዲሁም እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ የመቀመጫ ወይንም ወንበር ቁጥራቸውን ማወቅ ይችላሉ።

አገልግሎቱ ይህን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም የማይችሉትን ታሳቢ አድርጓል። በዚህም ሂደትም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን የማያውቁ ተገልጋዮች አጠገባቸውን ወደሚገኙ ባንኮችን በመሄድ አገልግሎቱን በቀላሉ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

የፀጥታ መደፍረስን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ችግሮች ከተከሰቱን አገልግሎት አሰጣጡ ላይ እክል የተፈጠረ እንደሆነም፣‹‹አስቀድሞ ፈጣን በሆነ መልኩ ውድ ደንበኞቻችን በድንገተኛ ችግሮች ምክንያት አገልግሎት የማንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን›› የሚል መልእክት ለተገላጋዮች ያደርሳል። ይህን መልእክት በመላክም ደንበኞች መረጃ ሳይኖራቸው ለእንግልት እንዳይዳረጉ ያደርጋል።

አውቶቡሶቹ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ዘመናዊ ካሜራዎች ተገጥሞላቸዋል። ማንኛውም ሰው አውቶቡስ ውስጥ በሚገባ ጊዜ የገባውን የሰው ቁጥር ይመዘግባሉ። ተጠቃሚዎች ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን ባትሪ መሙላት ከፈለጉም በተቀመጡበት መከወን ይችላሉ። የዋይ ፋይ ሲስተም የተገጠመላቸው በመሆኑ ተጠቃሚዎች የፈለጉትን መረጃም ሆነ መዝናኛ በቀላሉ ማግኘትና ዘና ብለው ከፈለጉበት መድረስ ይችላሉ።

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ ገለፃም፤ ይሄን በአገር አቅም በአገር ልጆች በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የተሰሩ መሆናቸው አውቶቡሶቹን ልዩ ያደርጋቸዋል። እንደ አገርም ለኢትዮጵያ ኩራት ነው። አገር ውስጥ የተመረቱ እንደመሆናቸውም በግዢ ሂደት ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ማዳን ተችሏል።

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በቀጣይም ዘመናዊ የሆኑና ‹‹safety device›› የተገጠመላቸው ማለትም አደጋን በቀላሉ መከላከል የሚያስችል ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ለመስጠት አቅድ ይዟል። ካርበን ልቀት ነጻ የሆኑ፣ ነዳጅን የማይጠቀሙ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ አውቶብሶችን በመጠቀም ለነዳጅ ግዥ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረትም ይሰራል።

እንደ ወይዘሮ ፍሬህይወት ገለፃም፤ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ የአገልግሎት አድማሱን እያሰፋ በእድገት ላይ እድገት እያስመዘገበ መጓዙ የመላ ሰራተኞች የጋራ ቅንጅትና ስራ እንዲሁም ብቃት ውጤት ነው።

በእለቱ ዘመናዊዎቹን የምድር አውሮፕላኖች የጎበኙ የድርጅቱ ሰራተኞች፣ በተመለከቱት እጅጉን ደስተኛ መሆናቸውን ገልፀዋል። ለድርጅቱ ስኬታማ ጉዞ አመራሩ እየሰራ የሚገኘውን ስራ በማድነቅም፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በቀጣይም ከዚህ በላቀ ከፍ ብሎ እንዲታይ እጅ ለእጅ ተያይዘው እንደሚሰሩ ቃል ገብተዋል። ህብረተሰቡም ዘመናዊ አውቶቡሶቹ ከፍ ሲል እንደ አገርና ዝቅ ሲል እንደ ራስ በጥንቃቄ ሊገለገልበት እና ሊንከባከበው እንደሚገባም መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# “አባቱ ደጀን እናቱ ጣና፤ - የኢትዮጵያ ልጆች መጡ እንደገና ፤...”

የሐሙስ ምሽት ነሐሴ 5 ቀን 2014 ዓ.ም ፋና 90 ዜና ከወትሮው በተለይ በጋሽ አበራ ሞላ /አርቲስት ስለሽ ደምሴ ዘመን ተሻጋሪ የትውልድ ዜማ “አባቱ ደጀን...፣”ን ከፊት በማስቀደም ነው የጀመረው ። ዕለቱን የዋጀ ስልት ሆኖ ነው የተሰማኝ ። አዎ!

**“አባቱ ደጀን እናቱ ጣና ፣**
**የኢትዮጵያ ልጆች መጡ እንደገና ፤... “**

ስምን መልዓክ ያወጣዋል እንዲሉ “ታላቁ የኢትዮጵያ ‘ሕዳሴ’ ግድብ፤” የተባለው እኮ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እንደገና ኃይላቸውን እንደ ንስር አድሰው በከፍታ መምጣትን ለማብሰርም አይደል።

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እንደ ስሙ አንድምታው ከኢኮኖሚያዊ አውታርነት አድማስ ባሻገር ነው። የኢትዮጵያን የሕዳሴ ጉዞ የለኮሰ ብቻ ሳይሆን የሕዳሴውን ማርሽም የቀየረ የተዋጣለት ሹፌርም ነው። ከሁለት አመት በኋላ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ የብርሃን ጭላንጭል ለናፈቃቸው ከ50 ሚሊየን በላይ ወገኖች ጸዳል ሊሆን አሽቷል። በተደጋጋሚ በሚከሰት የኃይል መቆራረጥና እጥረት አሳሩን እየበላ ለሚገኘው ኢንዱስትሪም ሆነ ሌላ የኢኮኖሚ ዘርፍ የምስራች ይዟል። የኤሌክትሪክ ኃይል በመሸጥ በአመት ከ1 ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘትም አልሟል። ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ በቀጣናው ከፍ ሲልም በአፍሪካም ሆነ በዓለም የሚኖራትን ጂኦፖለቲካዊ ተጽዕኖ ከፍ ያደርጋል። ይህ አንድ ላይ ሲደማመር ለኢትዮጵያ ሕዳሴ መበሰር ነጮች እንደሚሉት የመስፈንጠሪያ ሰሌዳ /spring- board/ ይሆናል። ገጥሞት ከነበረው የለየለት ክሽፈት በለውጡ አመራር ቆራጥ ውሳኔ ድኖ ለዚህ መብቃቱ ታላቅ ገድል ነው።

የኢትዮጵያ ሕዳሴ ወሳኝ መታጠፊያ /critical juncture/ የሆነው ይህ ግዙፍ ሕልምና ራእይ እውን ሆኖ ከአንድም በሁለት ተርባይን በአሁናዊ አቅሙ 550 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የበቃው በመላው ኢትዮጵያዊ ርብርብ ነው። ከሊስትሮ እስከ እንጨት ለቃሚ፤ ከሕጻናት እስከ አረጋውያን፤ ካጣ ከነጣ ድሃ እስከ ባለጠጋና ባለሀብት፤ ከአገሬው እስከ ዲያስፓራው፣ ወዘተረፈ ጠጠር ያልጣለ የለም። ከእለት ጉርሱ ቀንሶ፣ ከልጆቹ ጉሮሮ ቀምቶ የታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ ገዝቷል። ገንዘብ አበርክቷል። ለግሷል። ጉልበቱንና እውቀቱን አዋጥቷል። ከፍ ሲልም ሕይወቱን ሰውቷል። በድምሩ ወደ 20 ቢሊየን ብር የሚጠጋ አዋጥቷል።

በአገሪቱ ታሪክ ኢትዮጵያዊ በሞላ ያለ ልዩነት እስላም ክርስቲያን፤ አማራ ኦሮሞ ትግሬ ጉራጌ ሃድያ፤ ሳይል በአንድነት ሰራዊትና ደጀን የሆነለት ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። በነገራችን ላይ በአገሪቱ ታሪክ በብዙ ሚሊየን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ለአንድ ሜጋ ፕሮጀክት ይሄን ያህል ገንዘብ አዋጥተው አያውቁም። በአሜሪካ ኦሪገንና በኮሎምቢያ ካሊ አትሌቶቻችን በነጠላም ሆነ በቡድን እንደ አገር ክብረወሰኑን እንደሰባበሩት መላ ኢትዮጵያዊ ደግሞ በሕዳሴው የቀደሙትን ትውልዶች ክብረ ወሰን ሁሉ ሰባብረውታል። ተደቅኖበት ከነበረ የለየለት የክሽፈት አደጋ ታድጎ በእነዚህ ቀውጢና ፈታኝና እልህ አስጨራሽ አመታት ሁሉ ጥርሱን ነክሶ በአጭር ታጥቆና ህልቆ መሳፍርት ለሌለው ጫና አንድ ጊዜም ሸብረክ ሳይል ለዚህ ያበቃው በክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ የሚመራው የለውጥ ኃይልም ያለ ምንም ስስትና ንፍገት በልኩ እውቅና ሊቸረው ይገባል።

የእንችላለን መንፈስን ለኢትዮጵያውያን ከፍ ሲልም ለመላው አፍሪካ ያጋባው የሕዳሴው ግድብ ዳግማዊ ዓድዋ ነው። ካለምንም እርዳታና ብድር በዜጎች አበርክቶና በመንግስት በጀት እየተገነባ ያለ ተምሳሌታዊ ብሔራዊ ፕሮጀክት ነው። እስካሁን ከ163 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ የተደረገለት ሲሆን የሲቪል፣ የኤሌክትሪካልና የብረታ ብረት ገጠማው የስራ አፈጻጸም ከ83 በመቶ በላይ ደርሷል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ሁለተኛ ተርባይንን የኃይል ማመንጨትን ካስጀመሩ በኋላ ባስተላለፉት ጥልቅና ወካይ መልዕክት፤ “በታሪክ ውስጥ ማለፍና ታሪክ ሠርቶ ማለፍ የሚባሉ ሁለት ነገሮች አሉ። በታሪክ ውስጥ ማለፍ ዕድል፣ ታሪክ ሠርቶ ማለፍ ግን ዕድልም ድልም ነው። ይሄ ትውልድ በዓባይ ግድብ ጉዳይ ባለ ዕድልም ባለ ድልም ነው። የሺ ትውልድ ጥያቄ በሚመለስበት ዘመን ተገኝቶ ግድቡ ሲገደብ በዓይን ማየት፣ በእጅ መዳሰስ፣ በእግር መርገጥ ባለ ዕድል ሲያደርግ፤ ለግንባታው ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ከለገሡት፣ በዲፕሎማሲና በሚዲያ ለዓባይ ከሚከራከሩት፣ ታሪክ ሠሪ ጀግኖች ወገን መሆን ደግሞ ባለ ድል ያደርጋል። እነሆ አሁን የሕዳሴ ግድብ ከንድፍ አልፎ፣ ግንባታው ተገባድዶ፣ ግዙፍ ውኃ በጉያው ይዞ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ዛሬ ዓባይ ተረት ሳይሆን የሚጨበጥ እውነት ነው፤ ከዘፈን-እንጉርጉሮ ወጥቶ ኢትዮጵያን በብርሃኑ ሊያደምቃት፣ ኃይል ሆኖ ሊያበረታት ከጫፍ ደርሷል። በፈጣሪ እርዳታና በኢትዮጵያዊ ወኔ ሙሉ በሙሉ ግንባታውን አጠናቅቀን የልባችን እንደሚሞላ አልጠራጠርም። እንኳን ደስ ያለን!!”ብለዋል።

የሽብር ቡድኑ በአፈ ቀላጤዎቹ በኩል የዛሬ ሶስት አመት የኢትዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ተሸጧል እያለ ሲያናፋ፤ ኢትዮጵያውያን ግን የመጀመሪያውን የውሃ ሙሊት ሐምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ እንዲይዝ አድርገዋል። ሁለተኛው የውሃ ሙሊት ደግሞ ባለፈው ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም 13 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በመያዝ ተጠናቋል። ሟርተኛውና አሸባሪው ሕወሓት ተሸጧል ያለው ይህ አገራዊ ግዙፍ የብርሃን እሸት የምስራች እንካችሁ ብሏል። ካለፈው የካቲት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በአንድ ተርባይን ብቻ 275 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። የሁለተኛው ተርባይን ደግሞ ባለፈው ሀሙስ 275 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ሶስተኛው የውሃ ሙሊት ደግሞ በበነጋው ዓርብ ተጠናቋል። ግድቡ የያዘው የውሃ መጠንም ወደ 22 ቢሊየን ሜትር ኩብ አድጓል። የቀሪዎቹ ተርባይኖች ገጠማ፤ የግድቡ ግንባታና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራዎችም በሁለት አመት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ 3ኛ ዙር የውሃ ሙሌት ባለፈው ዓርብ ረፋድ በድል መጠናቀቁን በግድቡ ቦታ ተገኝተው ሲያበስሩ፤ “የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ ደስ የሚያሰኝ ታላቅ ድል ነው። ሆኖም ዓባይ ለኢትዮጵያ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ለዓለም ተሰጥቷል።” ብለዋል፤ በክቡር ጠቅላይ ሚንስትር አመራር ግድቡ ገጥመውት የነበሩ ስር የሰደዱ ብልሹ አሰራሮች፣ ሙስናና ደካማ የኮንትራት አስተዳደር ተለይተው የእርምት እርምጃ መወሰዱ ታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ከክሽፈትና ከለየለት ውድቀት ከመታደግ አልፎ ለኢትዮጵያውያን እራትና መብራት ሊሆን ሁለተኛ እሸት አቅምሷል። የግብፅን የሱዳንን የአሜሪካና የምዕራባውያንን የአረብ ሊግን አለማቀፍ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጫናን በጥበብና በማስተዋል በመቋቋም እና ግብፅ የግድቡን ጉዳይ የዓለም የደህንነትና የሰላም ስጋት አድርጋ ለማሳየት መጀመሪያ ራሷ በኋላ በአረብ ሊግ አይዞሽ ባይነት ቱኒዚያን በመጠቀም ጉዳዩን ከአፍሪካ ሕብረት በማውጣት ወደ መንግስታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት አጀንዳነት ለማሳደግ ያደረገችው ጥረት አገራችን በጥብቅ ዲፕሎማሲያዊ ዲስፕሊንና በጥበብ በተመራ ዓለም አቀፍ ግንኙነት አገራትን ከጎኗ በማሰለፍ የተደገሰላት ደባ እንዲከሽፍ ከማድረጓ ባሻገር የግድቡ ጉዳይ የተፋሰሱ አገራትና የአፍሪካ ሕብረት እንጂ የመንግስታቱ ድርጅት አለመሆኑን ማረጋገጥ ችላለች።

ድርድሩም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አፍሪካ ሕብረት ተመልሷል። ምንም እንኳ ግብጽና ሱዳን ሰበብ አስባብ እየደረደሩና ፍላጎታቸውን በሌላ መንገድ ለማራመድ ላይ ታች እያሉ ቢሆንም። ጣልቃ ለመግባት አሰፍስፈው የነበሩ ምዕራባውያንም እርማቸውን እንዲያወጡ አድርጋለች። ሆኖም ዛሬም ሆነ ጥንት ግብፅ አልተኛችልንም። ዓባይን ከመነሻው ለመቆጣጠር ከ11 ጊዜ በላይ ልትወረን ልታስገብረንና ቅኝ ልትገዛን ሞክራ እንዳልተሳካላት የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። በዲፕሎማሲው መድረክ ብትረታም በሱዳን አማካኝነት የውክልና ጦርነት ከፍታ መሬታችንን አስወርራለች። አገርን ለከዱ ጡት ነካሾች የገንዘብ የጦር መሳሪያ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ድጋፍ በማድረግ አገራችንን ወደ ለየለት ቀውስና ትርምስ ለመክተት ቀን ከሌት እየሰራች ነው። ይህን የተገነዘቡ ኢትዮጵያውያንም ልዩነታቸውን ትተው በአንድነት አገራቸውን ከውስጥ ተላላኪዎችና ከውጭ ጥቃት ለመከላከል ቀፎው እንደተነካ ንብ በአንድነት ተነስተዋል።

ግድቡ በአሁኑ ሰዓት ከ22 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በላይ ውሃ በመያዝ ራሱን መከላከል የሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ግብፅ ለዘመናት ኢትዮጵያ ሰላም ሆና አንድነቷ የሚጠናከርና ልማቷም የሚፋጠን ከሆነ አባይን ጨምሮ ገና የውሃ ሀብቷን ታለማለች በሚል በስጋት ላይ ያነጣጠረ ስጋት ከውስጥ ተላላኪዎቿ ጋር በመሆን ኢትዮጵያውያንን ለመበታተን ሰርታለች። በወንዝ በጎጥ የተከፋፈለች ደካማ አገር እንድትሆን ሌት ተቀን ሰርታም በተወሰነ ደረጃም ተሳክቶላታል። ዛሬም አሸባሪውን አልሻባብን ፣ ሕወሓት ሸኔንና ሌሎች ቅጥረኛ ምንደኞችን ተጠቅማ ከውስጥ እየወጋችን ነው ። ሆኖም የግብፅና የተላላኪዎቿ የቀን ቅዠት በጀግኖች ልጆቿ ይመከናል። እየመከነም ይገኛል። ሰሞኑን በምስራቁ የአገራችን ክፍል በሱማሌ ክልል በአልሻባብና በጭፍሮቹ ላይ የተወሰደው የማያዳግም እርምጃ ለዚህ ጥሩ አብነት ነው።

አይደለም ዛሬ ሶስተኛ ዙር ግድባችንን ሞልተን፣ ሁለተኛ የብርሃን እሸት ቀምሰን፤ ያለአንዳች ኮሽታ ብሔራዊ ምርጫ አካሂደንና በሚያስገርም ሁኔታ በአገራችን ተደቅኖ የነበረን ቀውስ ቀልብሰን፤ ከሶስት አመት በፊት በሴራ ፖለቲካ፣ በተላላኪውና በባንዳው የትህነግ ገዢ ቡድንና ተባባሪዎች ደባ በየእለቱ ቅርጹንና ይዘቱ እየቀያየረ በሚቀፈቀፍ ቀውስ መሀል ሆነን የጀመርነው አንደኛው የውሃ ሙሊት ዛሬ 3ኛ ዙር ደርሷል። ከዚህ በኋላ የሚቀሩን ሙሊቶችም ያለ ምንም ስጋት ይከናወናሉ። በዚህም ቅኝ ካለመገዛት ጋር ብቻ ተያይዞ የነበረውን ነጻነትና ሉዓላዊነት በኢኮኖሚያዊ በብልጽግና ለመድገም ጉዞዋን ጀምራለች። በድህነትና በተመፅዋችነት አንገታቸውን ደፍተው የነበሩ ዜጎች አንገታቸውን ቀና አድርገው በኩራት እንዲራመዱ የሚያደርግ ብሔራዊ (ፍላግሺፕ)ፕሮጀክት ባለቤት መሆን ችላለች።

ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ እንዳሉት በድህነትና በኋላ ቀርነት የሚማቅቅ ሕዝብ የተሟላ ሉዓላዊነት ሊኖረው አይችልምና። ስንዴ እየለመኑ፣ እየተመጸወቱ ሉዓላዊነቷን ያላስደፈረች፤ በነጻነት ታፍራና ተከብራ የኖረች ብሎ መመጻደቅን ድሉን ሙሉእ አያደርገውም። መቼም አሸባሪው ትህነግ ለዘረፋና ለስልጣን ሲል የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ በመስጠትና በሌብነት ጥርሱን የነቀለበት ስለሆነ እሱ እንደሚያደርገው ግድቡ ተሸጧል ቢል የሚያስገርም አይደለም። እሱ ሸጦት ስለነበረ አይደል ለአጠቃላይ ክሽፈት አንድ ሐሙስ ቀርቶት እያለ የለውጥ ኃይሉ ደርሶ የታደገው። በረሀብ ለተጎዱ ትግራዋይ ተልኮ እንደነበረው ስንዴ ከአንዴም ሁለት ሶስቴ ሸጦት የነበረውስ እሱ ራሱ ሕወሓት ነው። እንጨት ሸጣ ከልጆቿ ጉሮሮ ቀምታ መቀነቷን ፈታ የሰጠችውን ገንዘብ ከመስረቅ በላይ ግድቡን መሸጥ ምን አለ። ተራ የመጠጥ ውሃ ኤሌክትሮ ሜካኒካል እንኳ በቅጡ ገጥሞ ለማያውቅ፤ በብልሹ አሰራርና በሙስና ለበሸቀጠው ሜቴክ ያለ ጨረታ ከመስጠት በላይ ግድቡን መሸጥ ምን አለ?።

ያው ሁላችን እንደምናውቀው የትህነግ እፉኝት ቡድን ለፖለቲካዊ ጥቅምና ስልጣን ሲል ወላጅ እናቱንም ሆነ አገሩን እንደ አስቆርቱ ይሁዳ ከመሸጥ አይመለስም። ለትህነግ ፖለቲካ ማለት ብሔራዊ ጥቅምን አሲዞ መገበያየት፣ የንግድ ውል መፈጣጠም (Transactional) ነው። በዚህ የልቡና ውቅር (ማይንድሴት) ነው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ተሸጧል ሲል የነበረው። በፈጸመው ግፍና ክህደት በሰራው ስህተት በተናገረው ውሸት ወዘተረፈ ጸጸት የማያውቅና ያልፈጠረበት ሆኖ እንጂ ዛሬ ላይ በጸጸት ጸጉሩን በነጨ። እሱ እቴ ይገረማችሁ ብሎ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦልም ቢሆን እወርዳለሁ ያለ ጉድ እኮ ነው።

ሆኖም መጀመሪያ ሁለተኛውና ሶስተኛው የሕዳሴው ግድብ ውሃ ሙሊት፤ አሁን ደግሞ 2ኛው ዩኒት ኃይል ማመንጨት መጀመሩ የቀጣናውን ጂኦፖለቲክስ እንደ አዲስ በይኖታል። የግብፅን የውሃ ዲፕሎማሲና ፖለቲካም ከንቱ አድርጎታል። ለዚህ ነው ዛሬ አሸባሪውን አልሻባብና ሕወሓት ተጠቅማ አገራችንን ለመበቀል ሌት ተቀን እየሰራች ያለችው። ሱዳንን ግፊ የምትለው። ከ100 ሺህ በላይ ዜጎቻችን ከሳኡዲ አረቢያ መብታቸው ተገፎና ሰብዓዊ ክብራቸው ተዋርዶ እንዲወጡ ያሴረችው። የቀሩት በሳውዲ ማጎሪያዎች ታስረው እየማቀቁ ያሉት። ሆኖም ውሾች እየጮኹ ግመሉ ጉዞውን ያለማቋረጥ ቀጥሏል።

አገራችን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ፈጣሪ አብዝቶ ይባርክ ! አሜን ።

# ስፖርት

## ወርቃማዎቹ ወጣቶች ተሸለሙ

ብርሃን ፈይሳ

በኮሎምቢያ መዲና ካሊ ለስድስት ቀናት ሲካሄድ ቆይቶ ባለፈው እሁድ በተጠናቀቀው የዓለም ከ20 አመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተሳትፎ አንጸባራቂ ድል ያስመዘገበው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ልኡካን ቡድን ከትናንት በስቲያ ወደ አገር ቤት ተመልሷል። ቡድኑ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሲደርስ በከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመራሮች የጀግና አቀባበል ተደርጎለታል።

በአቀባበል ስነስርአቱ ላይ የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ ቀጀላ መርዳሳ፣ የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ እንዲሁም ሌሎች የስፖርቱ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች የተገኙ ሲሆን ለልኡካን ቡድኑ የአበባ ጉንጉን አበርክተዋል።

በትናንትናው እለትም ቡድኑ በክፍት አውቶብስ በተለያዩ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች እየተዘዋወረ ከሕዝብ ጋር ደስታውን ተጋርቷል። በስካይ ላይት ሆቴል በተዘጋጀ መርሃ ግብርም የእውቅናና የተለያዩ ሽልማቶች ተበርክቶለታል። በዚህም በቻምፒዮናው በ8 መቶ ሜትር የወርቅና በ1500 ሜትር የብር ሜዳሊያ በማጥለቅ የጎላ ስኬት የተጎናጸፈው አትሌት ኤርሚያስ ግርማ በልዩ ሁኔታ ከመንግስት 5 መቶ ሺ ብር ሽልማት ተበርክቶለታል። በተመሳሳይ የወርቅ ሜዳሊያ ላስመዘገቡ አትሌቶች ለእያንዳንዳቸው መንግስት የ3 መቶ ሺ ብር ሽልማት አበርክቷል። የብር ሜዳሊያ ያስመዘገቡ አትሌቶች የ2 መቶ ሺ ብር፣ የነሐስ ሜዳሊያ ያስመዘገቡ ደግሞ የመቶ ሺ ብር ተሸላሚ ሆነዋል። በቻምፒዮናው የዲፕሎማ ደረጃን ይዘው ያጠናቀቁ አትሌቶች የ50 ሺ ብር ሽልማት ሲሰጣቸው በውድድሮች ተሳትፈው ምንም ውጤት ያላስመዘገቡ አትሌቶች ለተሳትፏቸው የ30 ሺ ብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ቡድን መሪና ሌሎች ከቡድኑ ጋር የተጓዙ የስራ ሃላፊዎች ከ75 ሺ እስከ 30 ሺ ብር ድረስ ሽልማት አግኝተዋል።



ፎቶ፡- ሃዱሽ አብርሃ

ወጣቶቹ ባለ ድሎች በፌዴራል መንግስትና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፣

ከፌደራል መንግስት በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ለስኬታማው የወጣቶች አትሌቲክስ ቡድን የተለያየ መጠን ያለው የገንዘብ ሽልማት አበርክቷል። በዚህም የወርቅና የብር ሜዳሊያ ያጠለቀው አትሌት ኤርሚያስ ግርማ የ250 ሺ ብር ተሸላሚ ሆኗል። የወርቅ ሜዳሊያ ያስመዘገቡ አትሌቶች የ150 ሺ ብር ሽልማት ከከተማ አስተዳደሩ ሲበረከትላቸው የብር ሜዳሊያ ያጠለቁ የመቶ ሺ ብር፣ የነሐስ ሜዳሊያ ላሸነፉ ደግሞ የ75 ሺ ብር ሽልማት ተበርክቷል።

በሽልማትና እውቅና መርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ ቀጀላ መርዳሳ ባደረጉት ንግግር፣ የኢትዮጵያ ስፖርት ቀደም ከነበረው መቀዛቀዝ ወጥቶ በዘንድሮው አመት ውጤታማ የሆነ አንጸባራቂ ድል እየተመዘገበበት እንደሚገኝ ገልጸዋል። በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች የኢትዮጵያ ገጽታ ከፍ ያለበትና ሕዝብንም ያኮራ ድል መመዝገቡን ያስታወሱት ሚኒስትሩ፣ የታላላቆቻቸውን ፈለግ ተከትለው ወጣቶቹ አትሌቶች 12 ሜዳሊያዎችን አስመዝግበው በመመለሳቸው የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል። መንግስት ብቁ፣ አሸናፊና ተተኪ አትሌቶችን በማፍራት ረገድ ያስቀመጠው የትኩረት አቅጣጫ ስኬታማ በመሆኑ ውጤቱ እንደተመዘገበም ሚኒስትሩ አክለዋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አገኘው ተሻገር በበኩላቸው "ኢትዮጵያና አትሌቲክስ የማይነጣጠሉና የተጋመዱ ናቸው" በማለት ይህ የውጤታማነት ጉዞ ከቀጠለ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል ገልጸዋል። ለዚህም መንግስት ከአትሌቶች ጎን በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል ገብተዋል።

ኮማንደር ደራርቱ ባደረገችው ንግግርም፣ እንዳለፈው ቶኪዮ ኦሊምፒክ ፌዴሬሽኑ ጣልቃ ገብነት ሳይኖርበት በመናበብ መስራቱ ለአንጸባራቂው ውጤት መመዝገብ ዋነኛ ምክንያት መሆኑን ተናግራለች። የአትሌቶች ተወካይ የሆነችው አትሌት መሰለች መልካሙ ለተደረገው ደማቅ አቀባበል ምስጋና በማቅረብ፣ ወጣቶቹ ያስመዘገቡት ድል በቻምፒዮናው ታሪክ ለኢትዮጵያ ትልቁ ውጤት መሆኑን አስታውሳለች። ወጣቶቹ አትሌቶች በውድድር ወቅት ከአሰልጣኞቻቸው የሚሰጣቸውን ምክር ተግባራዊ በማድረግና እንደ ታላላቆቻቸው በመተባበር ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ተወጥተው ስኬታማ መሆን እንደቻሉ ተናግራለች። ይህም ታዳጊዎች ላይ መስራት እንዳለበት ማሳያ መሆኑን ጠቁማ ለወጣቶቹ አትሌቶች በቀጣይ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግ ጠይቃለች።

የወጣት አትሌቲክስ ቡድኑ በውድድሩ ታሪክ 6 ወርቅ፣5 ብርና 1 የነሐስ ሜዳሊያ በማስመዝገብም ከዓለም ሶስተኛ ከአፍሪካ ደግሞ ቀዳሚ ሆኖ ማጠናቀቅ ችሏል። በ19 አትሌቶች በሁለቱም ፆታ በ10 የውድድር ተግባራት ብቻ የተሳተፈው የአትሌቲክስ ቡድን በድምሩ በ12 ሜዳልያዎች ያስመዘገበ ሲሆን ከአንድ አትሌት በስተቀር ሜዳሊያ ያላገኙ አትሌቶች የዲፕሎማ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል። ይህም ቡድኑ ከዓለም አገራት አሜሪካንንና ጃማይካን ተከትሎ 3ኛ ደረጃን ይዞ እንዲያጠናቅቅ አስችሎታል።

በዚሁ ቻምፒዮና በ1500 ሜትር የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ የቻለው ወጣቱ አትሌት ኤርሚያስ ግርማ በ800 ሜትር ተጨማሪ ወርቅ በማጥለቅ በቻምፒዮናው የጎላ ኢትዮጵያዊ አትሌት ሆኗል። በ3ሺ ሜትር መሰናክል ወንዶች ሳሙኤል ዱጉና የወርቅ ሜዳሊያውን ሲያጠልቅ ሌላኛው ኢትዮጵያዊ ወጣት አትሌት ሳሙኤል ፍሬው በድንቅ ብቃት የብር ሜዳሊያውን ወስዷል። ከባድ ፉክክር ባስተናገደው በ5ሺ ሜትር ሴቶች ውድድር መዲና ኢሳና መልክናት ውዱ በተመሳሳይ ወርቅና ብር ሜዳሊያ ሲያጠልቁ፣ በ1500ሜ ሴቶች ደግሞ በአትሌት ብርቄ ሀየሎም (4:04.27) የቻምፒዮናውን ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር የወርቅ ሜዳሊያ ማሸነፍ ችላለች። በ5ና 3ሺ ሜትር ወንዶች በአዲሱ ይሁኔና መልኬነህ አዘዝ የወርቅ፣ በ3ሺ ሜትር መሠናክል ሴቶች በሲምቦ አለማየሁ፣ በ1500 ሜትር ወንዶች በኤርሚያስ ግርማ እና በ3ሺ ሜትር ሴቶች በፅዮን አበበ የብር ሜዳሊያዎችን ያሸነፈች ሲሆን፣ በተጨማሪም በሴቶች 3ሺ ሜትር መሰናክል በአትሌት መሰረት የሻነህ የነሀስ ሜዳሊያ ማግኘቷ ይታወቃል።


### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| የአመልካች ስም እና አድራሻ: ሻንክሲ ያንቻንግ ፔትሮሊየም ግሩፕ ራበርኮ ሊሚትድ (SHAANXI YANCHANG PETROLEUM GROUP RUBBER CO.,LTD) አድራሻ: FENGHE AREA,QINDU DISTRICT,XIANYANG, SHAANXI,CHINA | | |
| የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ:የቃል እና የምስል | | |
| NEOLIN | ማመልከቻ ገቢ የሆነበት ቀን | የማመልከቻ ቁጥር |
| | 30/11/2020 | FTM/0001/012130 |
| ዓለም አቀፍ ምድብ፡-12 | | |
| ማመልከቻ የሚሸፍናቸው ምርቶች | | |
| **ምድብ 12**፡- የውስጥ ቱቦዎች ለኒዩማቲክ (pneumatic) ጎማዎች, ለተሽከርካሪ ጎማዎች ጠንካራ ጎማዎች, ኒዩማቲክ (pneumatic) ጎማዎች; ጎማዎችን እንደገና ለማንበብ መረጣዎች; ፀረ-መንሸራተት ሰንሰለቶች; ለተሽከርካሪ ጎማዎች ሪምስ (rims) የተሽከርካሪ ጎማ ጎማዎች, ለተሽከርካሪ ጎማዎች መገናኛዎች, የመኪና ጎማዎች [ጎማዎች]; ኤሮታየሮች (aero tyre) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃውሞ ያለው ሰው የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ካላቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ባለቤቱ ሳይፈቅድ በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክቱን ቢገለገል ወይም ባለቤቱ በንግድ ምልክቱ ላይ ያለውን ማንኛውም ዓይነት መብቱን የሚጋፋ ተግባር ሲፈጽም ቢገኝ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ክስ እንደሚመሰረትበት እናሳውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

ADDIS ZEMEN VOI-LXXXI No-338 08/12/2014 (14/8/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| **የአመልካች ስም እና አድራሻ**: ዜጂያንግ ጂንሺ ቴክስታይል ቴክኖሎጂ ኮ ሊሚትድ (ZHEJIANG JINSHI TEXTILE TECHNOLOGY CO., LTD.) አድራሻ፡ INDUSTRIAL PARK, HONGQIAO TOWN, CHANGXING COUNTRY, HUZHOU CITY, ZHEJIANG PROVINCE, CHINA., HUZHOU People's Republic of Korea. | | |
| የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ፡ቃል | | |
| JSHION | ማመልከቻ ገቢ የሆነበት ቀን | የማመልከቻ ቁጥር |
| | 20/12/2021 | FTM/0001/013060 |
| ዓለም አቀፍ ምድብ፡-25 | | |
| ማመልከቻ የሚሸፍናቸው ምርቶች | | |
| **ምድብ 25**፡- ልብስ፣ ኮፍያዎች፣ የጭንቅላት ልብሶች፣ የውስጥ ልብስ፣ ሻውል፣ ጓንት [ልብስ]፣ ሆሲየሪ፣ የአንገት ቧንቧ ሸርተቴዎች፣ መሀረብ፣ ጫማ፣ ሸፋኖች [ልብስ] | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃውሞ ያለው ሰው የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ካላቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ባለቤቱ ሳይፈቅድ በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክቱን ቢገለገል ወይም ባለቤቱ በንግድ ምልክቱ ላይ ያለውን ማንኛውም ዓይነት መብቱን የሚጋፋ ተግባር ሲፈጽም ቢገኝ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ክስ እንደሚመሰረትበት እናሳውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

ADDIS ZEMEN VOI-LXXXI No-338 08/12/2014 (14/8/2022)

### ያገለገሉ መኪኖች ጨረታ ማስታወቂያ

ሄጦሳ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን ኃ. የተወሰነ ያገለገሉ መኪኖች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

1. ክላስ ኮመፓይን (Clas Combine) ኦሮ ሰሌዳ ቁጥር:-823
2. ክላስ ኮመፓይን (Clas Combine) ኦሮ ሰሌዳ ቁጥር:-824
3. Belarus ማራሻ እና መከሰከሻ ኮድ3 ሰሌዳ ቁጥር፡-109
4. አይዙዙ ፎርወርድ (IZUZU-Forward) ኦሮ ሰሌዳ ቁጥር:-35283
5 አይዙዙ ፎርወርድ (IZUZU-Forward) ኦሮ ሰሌዳ ቁጥር:-35284
6. ምስት ቡሽ (MISTI BUSHI) ኦሮ ሰሌዳ ቁጥር:-09512

በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማሟላት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን ያስታውቃል ፡፡

1) ተጫራቾች የማይመለስ ብር 500 በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ከሄጦሳ የገ/ሕ/ሥራ ዩኒየን ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 1(አንድ ) መግዛት የምትችሉ መሆኑና ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15 ተከታታይ የሥራ ቀን መግዛት ወይም መውሰድ ይችላሉ፡፡
2) ተጫራቾች በዚሁ የንግድ ዘርፍ የዘመኑ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ማቅረብ የሚችል፤
3) ተጫራቹ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የጨረታውን 10% በ CPO በማቅረብ መጫረት ይችላል፡፡
4) ተሽከርካሪዎቹን ጨረታውን ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ቀን እስከ ጠዋቱ 4፡00 ድረስ ሄጦሳ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን ዱቄት ፋብሪካ ጊቢ ማየት ይችላሉ፡፡
5) ጨረታው በ15ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ጀምሮ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሄጦሳ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን በሚገኘው የዩኒዬኑ ጽ/ቤት ውስጥ ይከፈታል፡፡
6) ዩኒየኑ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፡፡
7) ጨረታው በ15ኛው የሥራ ቀን ካልሆነ ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዚሁ ዕለት 4፡30 በላይ ይከፈታል፡፡
8) ተጫራቾች የግልም ሆነ የመንግሥት ድርጅት የድርጅቱን ውክልና መቅረብ አለበት፡፡
9) ተጫራቹ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ 5 የሥራ ቀን ውስጥ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ ማሽኑን መውሰድ አለበት፡፡
10) ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በዩኒየኑ ጽ/ቤት በመገኘት ወይም /በስልክ ቁጥር፡-0223350888/0223350936 መረዳት ይችላሉ፡፡

አድራሻችን :- ሔጦሳ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን አርሲዞን ሔጦሳ ወረዳ ኢተያ ከተማ ኖክ ማደያ ከፍ ብሎ፡፡

ስልክ ፡-0223350936 ስልክ ፡-0911840518/0912959618

**በአርሲ ዞን ሄጦሳ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን ኃ.የተወሰነ**